# የኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ

መጋቢት 2017

አዲስ አበባ

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 2
2. የፖሊሲው መነሻዎች ........ 3
3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ መርሆዎች እና ዓላማ ........ 5
4. የፖለሲ ጉዳዮችና አቅጣጫዎች ........ 7
   - 4.1 የሀገር ውስጥ ንግድ ሥርዓት ........ 7
   - 4.2 የገቢና ወጪ ንግድ አስተዳደር ማዕቀፍ ........ 10
   - 4.3 የሸማቾች መብት ጥበቃ እና ፍትሃዊ ንግድ ........ 12
   - 4.4 ብዝሃ-ዘርፍ የወጪ ንግድ እና ተወዳዳሪነት ........ 15
   - 4.5 በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር ዉስጥ መሳተፍ ........ 18
   - 4.6 ከባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ግንኙነት እና ኢኮኖሚያዊ ውህደት ........ 20
   - 4.7 የገቢና ወጪ ንግድ ማሳለጥ ........ 22
   - 4.8 የገበያ መሰረተ ልማት ማስፋፋትና ማዘመን ........ 25
   - 4.9 ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ........ 27
     - 4.9.1 ስርዓተ ጾታ ........ 27
     - 4.9.2 የአየር ንብረት ለውጥ ........ 28
     - 4.9.3 ስራና ሰራተኛ ........ 28
     - 4.9.4 የአካል ጉዳተኛ አካታችነት ........ 29
     - 4.9.5 ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ........ 30
5. ቁልፍ የፖሊሲ ውጤቶች ........ 30
6. የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ........ 33
   - 6.1 ፈፃሚ ተቋማት ........ 33
   - 6.2 የህግ ማዕቀፍ ........ 35
   - 6.3 ልማት ፕሮግራሞች ........ 35
   - 6.4 የፖሊሲ ክትትልና ግምገማ ........ 38
7. ፖሊሲውን የማውጣት ስልጣን እና የፖሊሲው ወሰን ........ 41
8. ተያያዥ ፖሊሲዎች ........ 41
9. የቃላት ፍች ........ 43

## 1. መግቢያ

ባለፉት አስር ዓመታት በሀገራችን ለተመዘገበው ፈጣንና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ ልማት የንግድ ዘርፍ የተጫወተው ሚና እና ያበረከተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው፡፡ የንግድ ዘርፉ በአንድ በኩል ለአጠቃላይ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትና ልማት የላቀ ድርሻ የሚያበረክትና የዕድገት አንቀሳቃሽ፤ በሌላ በኩል ሥር የሰደዱ ችግሮች በተለይም ዘርፍ የሚመራበት ራሱን የቻለ ፖሊሲ ባለመኖሩ የገቢ ንግዱ ወጥ በሆነ እሳቤ እና አደረጃጀት የሚመራ አለመሆኑ እንዲሁም የወጪ ንግዱም ቢሆን በበርካታ ተቋማት የሚመራ እና ቅንጅትና መናበብ የሚጎለው ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የንግድ ሥርዓታችን ፍትሃዊ ውድድር የሚጎድለው፤ የተለያዩ ህገ-ወጥነትና ብልሹ አሰራሮች የበዙበት፤ ሸማቾችን ያማረሩ የግብይት ሁኔታዎች የሚስተዋሉበትና በዓለም አቀፍ ገበያም ተወዳዳሪነትን ያላረጋገጠ ዘርፍ ነው፡፡ ንግድን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮች በሌሎች ሴክተር ፖሊሲዎችና በተለያየ ጊዜ በሚወጡ አዋጆችና ደንቦች ውስጥ በተበታተነ ሁኔታ መገኘታቸው ዘርፉን በተሟላ ሁኔታ ለመምራትና ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት አስቸጋሪ አድርጎት ቆይቷል፡፡

ይህንኑ ክፍተት በመገንዘብ ባለፉት ዓመታት ዘርፉን ለማዘመንና ተወዳዳሪ ለማድረግ ሲከናወኑ ከቆዩት የንግድ ሪፎርም አጀንዳዎች መካከል በዘርፉ የሚታዩ መሠረታዊ ችግሮችን ለመፍታትና ዓለም አቀፍ ተወደደሪነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ብሔራዊ ፖሊሲ እንዲኖረው ማስቻል ትኩረት ተሠጥቶት ዝግጅቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የንግድ ፖሊሲ ሀገራዊ የብልፅግና ራዕይ ለማሳካት ጉልህ ሚና ያለውን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ እና የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

ፖሊሲው መንግሥት በሀገር ውስጥና በውጭ ንግድ መስኮች ለሚተገበራቸው አጀንዳዎች እና ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ግልፅ አቅጣጫዎችን የሚያመላክት ነው፡፡ የዘርፉ ቁልፍ ተዋናይ የሆነው የግሉ ዘርፍም ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም አቀፍ የንግድ ምህዳር ውስጥ ወጥነት ባለውና ተገማች በሆነ የፖሊሲ ከባቢያዊ ሁኔታ ውስጥ ሥራውን መምራትና ማስተዳደር እንዲችል ጭምር በፖሊሲው ትከረት ተሠጥቶታል፡፡

በሌላ በኩል ሀገራዊ የንግድ ፖሊሲው የተቀረፀው በአገራችን እየተገነባ ባለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሲሆን የግሉን ዘርፍ ዋነኛ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጎ በመውሰድና መንግሥት ለግሉ ዘርፍ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር የገበያ

ክፍተት ባለባቸውና በተመረጡ ወሳኝ የኢኮኖሚ መስኮች የሚኖረውን የተመረጠ ጣልቃ የመግባት ሚናውን ከግምት በማስገባት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ ፖሊሲ የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት የሚመራ እንደመሆኑ መጠን ቀጣይ የንግድ ድርድሮችን፣ ስምምነቶችን ፣ ውህደትን፣ ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን እና የንግድ ሰንሰለት ነባራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ፖሊሲው ሀገራችን ቅድሚያ ትኩረት በምታደርግባቸው እና የዓለም አቀፍ ንግድ ትኩረት የሆኑትን ምርትና አገልግሎቶች እንዲሁም የአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፎች እና በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ወሳኝ በሆነው የንግድ ሰንሰለቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ፖሊሲው የንግድን ብዝሃ-ዘርፍ (multi-sectoral) ባህሪ ታሳቢ ያደረገ የፖሊሲ ቅንጅትንና ወጥነትን ለማረጋገጥ ከሌሎች ሀገራዊ ፖሊሲዎች እንዲሁም ቀጣናዊና አህጉራዊ የንግድ ትስስር አጀንዳዎች ጋር እንዲተሳሰር ተደርጓል፡፡ ከላይ የተገለፁትን የፖሊሲውን መሠረታዊ እይታዎች እውን ለማድረግ ለሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ የንግድ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡ፖሊሲው በዋናነት መግቢያ፣ የፖሊሲ መነሻዎች፣ የፖሊሲ አስፈላጊነት፣ መርሆች፣ዓላማዎች፣የፖሊሲ ጉዳዮችንና ዋና ዋና አቅጣጫዎችን፣ ቁልፍ የውጤት መስኮችን፣ የፖሊሲውን ወሰን፣የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልቶችን፣ ሌሎች ተዛማጅ ፖሊሲዎች እና የቃላት ፍችን ይዟል፡፡

## 2. የፖሊሲው መነሻዎች

የኢትዮጵያ የልማት እቅድ ዘላቂ፣ ፈጣን፣ ሰፊ መሰረት ያለውና አካታች የሆነ ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ንግድን በማስፋፋት እና የወጪ ምርት አይነቶችና የመዳረሻ ገበያዎችን በማሳደግ የአፍሪካ የብልፅግና ሞዴል መሆን ነው፡፡ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግስት በኢኮኖሚ እድገት ላይ የያዛቸው ዕቅዶች መሰረት የሚያደርጉት ባለፉት አመታት የታዩትን ተግዳሮቶች በማጤን እና የኢኮኖሚውን ልዩ ሁኔታዎች እና በቀጣይ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ልዩ ባህርይ ያላቸውን እንደምታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

የንግድ ስራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቀደምት እና የኢኮኖሚ ማዕከል ሆኖ የቆየ ቢሆንም እስከ አሁን የሀገሪቱን የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓትን በአግባቡ የሚመራ ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ሀገራዊ የንግድ አሰራር ሁኔታ በንግድ ከባቢው እና በኢንቨስትመንት ልማት ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ የንግድ ሥርዓቱ በበርካታ ተግዳሮቶች ውስጥ ያለ ሲሆን ለአብነት ያህል፤ የገቢ ንግዱ ወጥ በሆነ እሳቤ እና አደረጃጀት እየተመራ አለመሆኑ እና የወጪ ንግዱም ቢሆን በተበታተነ ሁኔታ በበርካታ ተቋማት የሚመራ እና ቅንጅትና

መናበብ የሚጎለው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የንግድ ሥርዓታችን ፍትሃዊ ውድድር የሚጎድለው፤ የተለያዩ ህገ-ወጥነትና ብልሹ አሰራሮች የበዙበት፤ ፍላጎት መር የገበያ ሥርዓት በመለመዱ ለዋጋ ግሽበት በር የከፈተ መሆኑ፣ ሸማቾችን ያማረሩ የግብይት ሁኔታዎች የሚስተዋሉበት፣ የሀገራችን ምርት በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ተገማች የሆነ የገበያ እድል አለመፈጠሩ፤ በዓለም አቀፍ ገበያም ተወዳዳሪነትን ያላረጋገጠ፣ ለምርትና አገልግሎት ጥራት ትኩረት የማይሰጥ እንዲሁም ንግድን የሚያሳልጡ የሎጂስቲክ እና ትራንስፖርት ሥርዓቱ ቅልጥፍና እና ዘመናዊነት የሚጎድለው እና በዘርፉ ያሉ ህጎችና አሰራሮች በየጊዜው መለዋወጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ስለዚህ ይህ የንግድ ፖሊሲ ከላይ የተዘረዘሩትን መሰናክሎች በመፍታት እንዲሁም ከተለዋዋጭ የዓለም ንግድ ሁኔታ ጋር ማላመድ የሚያስችል ዘመናዊ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የንግድ ምህዳር ለማስፈን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በሀገር ውስጥና ዓለማቀፍ እሴት ሰንሰለት ትስስርን በማቀላጠፍ፤ ተወዳዳሪ የወጪ ንግድ እና ፍትሃዊ የሀገር ውስጥ ንግድ እና ሸማቾችን መብትና ጥበቃ ያማከለ የንግድ አውድ በመፍጠር፣ የወጪ ንግድ ገቢን ለመጨመር፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንዲሁም በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ለመዘርጋት እና የእውቀት ሽግግር ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ይህም ጠንካራ፣ ዘርፈ ብዙ፣ አስተማማኝ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ለመፍጠር እና በአፍሪካ የኢንቨስትመንት ማዕከል ለመሆን አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

የንግድ ፖሊሲው ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን የማሳደግ፣ ወጪ ንግድን የማስፋፋት እና የወጪ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠን እና በመዳረሻ ገበያ የማስፋት፣ ፈጠራንና ግልፅነትን የማበረታታት እና የንግድ እድሎችን ለማስፋት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ንግድ፣ በጠረፍ ንግድ ላይ እና በመዳረሻ ገበያዎች ያሉትን መሰናክሎችን በመቅረፍ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ፖሊሲው በሰራተኛው እውቀትና ክህሎት ለማሻሻል እና የተቀመጡ የአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ግቦችን እንዲሁም ለሴቶችና ወጣቶች በሚፈጠሩ የስራ እድሎች ላይ ያለመ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ለመፍጠር ያግዛል፡፡

በተመሳሳይ ሀገራችን የንግድ ግንኙነቷን ለማስፋት ከበርካታ መንግስታት የሁለትዮሽ ፣ቀጣናዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች ታደርጋለች፡፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ሰፋፊ ድርድሮችን በማካሄድ ላይ ትገኛለች፡፡ ሆኖም ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ ሰነድ ባለመኖሩ መንግስትና የንግዱ ህብረተሰብ ስለ ንግድ ህጎች፣ደንቦች እንዲሁም ስለ ዓለም

አቀፍ የንግድ እድሎች ያላቸው መረዳት እና እሳቤ አናሳ እንዲሆንና ሀገራችን በሚገባት ልክ ቀጣናዊና ዓለማቀፋዊ ንግድ ውስጥ ዋና ተዋናይ እንዳትሆን ምክንያት ሆኗል። ስለሆነም የንግድ ፖሊሲው የሀገሪቱን የንግድ ዘርፍ አሰራር፣ ድርድሮችን፣ ስምምነቶችን እንዲሁም ውህደትን ወጥ በሆነ እሳቤ ለመምራት የሚያስችል ነው።

በአጠቃላይ ይህ የንግድ ፖሊሲ የኢትዮጵያን የንግድ ሥርዓት የሚመራ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የኢኮኖሚውን ሂደት መልክ ብዙ በማድረግ አስተማማኝ እና ተጨባጭ የሆነ ልማት ለማምጣት የሚያገለግል ዋነኛ ማዕቀፍ ነው።

## 3. የፖሊሲው አስፈላጊነት፣ መርሆዎች እና ዓላማ

### 3.1 አስፈላጊነት

የንግድ ፖሊሲው በሀገራችን እየተስተዋሉ ያሉትን የንግድ ዘርፍ ስብራቶችን ለመጠገን፤ በዋነኛነት ወጥነት ያለው እና የተቀናጀ የንግድ ሥርዓት አመራር አደረጃጀት ለመፍጠር፣ ፍትሐዊ የሆነ የንግድ ውድድር አውድ ለመፍጠር፣ ለሀገራችን ምርቶች ሰፊና ተገማች የገበያ ዕድል ለማፈላለግ፣ የግብይት መሰረተ ልማት ችግሮችን ለመፍታት፣ የሎጅስቲክስና ገበያ ትስስር ችግሮች እና በዓለም አቀፍ የንግድ ሰንሰለት ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ ለማድረግ፤ በተመረጡ የገበያ ክፍተት ባለባቸው ዘርፎች የመንግስት ጣልቃ የመግባት ጠቀሜታን ቸል ባለማለት እና ክፍተቶችን ለመሙላት የሚደረገውን ጥረት ለማጠናከር ነው። በሌላ በኩል የሀገራችን የወጪ ንግድ በግብርና ምርቶች ያለውን ጥገኝነት በማላቀቅ የወጪ ምርትና አገልግሎት ብዝሃነት እና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚያስችሉ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም መንግስት በዚህ የንግድ ፖሊሲ ማሻሻያ አጀንዳ በመመስረት ተግዳሮቶችን ለመፍታት በንግድ ፖሊሲው የሚወሰዱ እርምጃዎችን ከፊሲካል፣ ሞኒተሪ እና የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ጋር በማጣጣም ለመስራት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

### 3.2 መርሆዎች

ንግድ በሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ግንባታ ያለውን ከፍተኛ ሚና ታሳቢ በማድረግ የዚህ ፖሊሲ ትግበራ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል።

- **ጥራት ተኮር፡-** በገበያው የሚቀርቡ ምርትና አገልግሎቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እና ጥራት ያለው የንግድ አገልግሎቶችን መስጠት።
- **ነፃ ገበያ፡-** በሁሉም ደረጃ የሚካሄዱ የንግድ አሰራሮች የነፃ ገበያ መርህን የተከተሉ ናቸው።

- **አካታችነት፡-** በሀገር ውስጥም ሆነ በወጪ ንግድ ሥራ ፍትሃዊ የሆነ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት እንዲሁም የተለየ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን አካላት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡
- **ተወዳዳሪነት፡-** የሀገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶች ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ እና የአምራቾችን ምርታማነት እንዲሻሻል በትኩረት መስራት፡፡
- **ግልጽነትና ተጠያቂነት፡-** የንግድ ህጎችና አሰራሮች ለሁሉም የንግድ ተዋናያን ግልፅ የሚሆኑበት እና የንግድ ህጎችና አሰራሮችን በሚያጎድፉ እና በሚጥሱት ላይ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፡፡
- **ተገማችነት፡-** የንግድ ህጎችና አሰራሮች ለሁሉም የንግድ ተዋናያን ተገማች መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡
- **ዓለማቀፋዊነት፡-** የንግድ ሥርዓቱ የዓለም አቀፍ ህጎችና ድንጋጌዎችን ባከበረ አግባብ መተግበር፡፡
- **አቅርቦት መር፡-** የምርትና አገልግሎቶች ግብይት ሥርዓቱ በዋናነት አቅርቦትን በሚያሳድግ አግባብ መምራት፡፡

### 3.3 ዓላማ

የኢትዮጲያ ንግድ ፖሊሲ አጠቃላይ ዓላማ ግልፅነት ያለው፣ አካታች እና በፍትሃዊ ውድድር ላይ የተመሰረተ የሀገር ውስጥ ንግድ እና ተወዳዳሪ የወጪ ንግድ በመገንባት ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለዘላቂ ልማትና ለሀገራዊ ብልፅግና መረጋገጥ ጉልህ አስተዋፅኦ ማበረከትና ከዓለም አቀፉ ንግድ ተገቢውን ድርሻ ማግኘት ነው፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች ፡-

1. ፍትሃዊ፣ተገማች፣ዘመናዊ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ የሀገር ውስጥ የንግድ ሥርዓት መገንባት፤
2. በዓለም አቀፋዊ እሴት ሰንሰለቶች (GVC) ውስጥ ጉልህ ተሳትፎን ማረጋገጥ፤
3. የወጪ ንግድ ብዝሃነትን እና ተወዳዳሪነትን በማጎልበት ሀገራዊ የወጪ ንግድ ገቢን ማሳደግ፤
4. በሁለትዮሽ፣ በአህጉራዊ አጋርነት እና በባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች ለኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎት የገበያ መዳረሻ ማሳደግ፤

5. የሀገራችን ምርትና አገልግሎት በዓለም ገበያ የሚኖራቸውን ድርሻ ማሻሻልና ሀገራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡፡

6. ዘመናዊ፣ ምቹና ቀልጣፋ የገበያ መሰረተ ልማት እና የንግድ ሎጂስቲክ መገንባት፤

7. የሸማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ የገበያ ውድድርን ለማስፈን፣

8. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ማዕከል ማድረግ፡፡

## 4. የፖለሲ ጉዳዮችና አቅጣጫዎች

በፖሊሲው መነሻ ሁኔታ እና አስፈላጊነት ላይ እንደተብራራው የሀገራችንን የንግድ ዘርፍ ስብራት በመጠገን ንግድ ለሀገራዊ ብልፅግና የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ትርጉም በሚሰጥ ደረጃ ለማሳደግ የሀገራችንን አወድ እና ዓለማቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታን ባማከለ መልኩ የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች መከተል አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የንግድ ፖሊሲው ከሌሎች የልማት ፖሊሲዎች ጋር በማስተሳሰር የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ ዋነኛ ድርሻ ያለው የዓለም አቀፍና ሀገር ውስጥ ንግድ ሥርዓትን የሚከተሉቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡

### 4.1 የሀገር ውስጥ ንግድ ሥርዓት

የንግድ ሥራን ለመጀመርና ህጋዊነትን ጠብቀው ለመሥራት ለዜጎች የሚሰጠውን ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች ለማዘመን፤ ሂደቶቹን ግልፅና ቀልጣፋ ለማድረግ ባለፉት ዓመታት የተተገበሩ የሪፎርም ሥራዎች መሻሻል ያመጡ ቢሆንም የንግድ ሥራን ለመጀመር እና ለማስኬድ ያለው አመቺነት ዓለም ከደረሰበት ደረጃ ለማድረስ ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ በአገራችን የሚካሄዱ የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ሥራዎች በአብዛኘው በኢ-መደበኛ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ዜጎች የሚበዙበትና እሴት የማይጨምሩ የድለላ ሥራዎች ጎልቶ የሚታዩበት በመሆኑ የንግድ ሥርዓቱ የተወሳሰበ፤ ግልፅነትና ፍትሃዊነት የጎደለው ሆኖ ቆይቷል፡፡

የተሣለጠና የተጠናከረ የሀገር ውስጥ የግብይት ሥርዓት መኖር ለውጭ ገበያና ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚመረተው ምርት እንዲያድግና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከዚህ አንፃር የሀገራችን የግብይት ሥርዓት መዋቅራዊ የሆነ የነፃ

ገበያ ውድድር ችግር ያለበት በመሆኑ የአምራቹንና ሸማቹን ተጠቃሚነት ሲፈታተን ቆይቷል፡፡ በተለይም የግብርና ምርቶች አምራች የሆነው አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ለሚያመርቷቸው ምርቶች ተገቢውን ዋጋ የማያገኙበትና ሸማቾች ደግሞ በተራዘመና ዕሴት በማይጨምር የግብይት ሰንሰለት ምክንያት በከፍተኛ ዋጋ የሚሸምቱበትና ለኑሮ ውድነት ፈተና ተጋልጦ የሚገኝበት ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡ የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ሥራዎች የሚከናወኑባቸው የግብይት ማዕከላት በአግባቡ ያልተደራጁ፣ የተሟላ የግብይት መሠረተ ልማትና ሎጂስቲክ እጥረትና ቅልጥፍና የሚጎድላቸው፣ ግልፅነት ያለው ትሥሥርና አሠራር የሌላቸው በመሆኑ የግብይት መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት የማያስችሉ፣ የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶችና አገልግሎቶችን ገበያ ውስጥ የበዙበትና ተቆጣጣሪ አካላት የምርቶችን ዱካ ለማወቅና ቁጥጥር ለማድረግ የሚቸገሩባቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ሀገራዊ ፋይዳና የዜጎችን ተጠቃሚነት ማዕከል በማድረግ የሀገር ውስጥ ንግድ ሥርዓት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልሎ እንዲቆይ መደረጉ በተወሰነ ደረጃ ዜጎች ሀብት እንዲያፈሩና ከዓለምአቀፉ የንግድ ሥርዓት ጋር እንዲተዋወቁ ዕድል የፈጠረላቸው ቢሆንም ከነፃ የገበያ ውድድር ሊገኝ የሚችለውን ቅልጥፍናና ጥቅም ያሳጠን መሆኑን በመገንዘብ የሀገር ውስጥ ገበያንና የውጭ ንግድን ደረጃ በደረጃ ለውጭ ባለሀብቶች የመክፈት እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡

በሀገር ውስጥ ንግድና ሥርጭት ሥርዓታችን ውስጥ ሥር ሰዶ የቆዩትን ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ማነቆዎች ከመፍታት አንፃር መንግሥት የሚከተሉትን የፖሊሲ እርምጃዎችንና አቅጣጫዎችን ይተገብራል፡፡

- የንግድ ዘርፍ ልማትን በሚመለከት መንግሥት በዋናነት በነፃ ገበያ መርህ የሚመራ የፖሊሲ አቅጣጫ የሚከተል ሆኖ ትርጉም ያለው የገበያ ክፍተት ሲያጋጥም፣ የአምራቹንና የሸማቹን መብትና ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል የገበያ ሁኔታ ሲኖር እንዲሁም ለሀገራዊ ልማትና ብልጽግና መረጋገጥ ያላቸው ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ስትራቴጅካዊ ሸቀጦችን በጥናት በመለየት ለአጭር ጊዜ የሚቆይ እና የዋጋና የሥርጭት ቁጥጥር ሥርዓት ሊተገበር ይችላል፣ እንዲሁም በገበያ መሸፈን ያልቻሉ፣ ሀብትና ጊዜ የሚጠይቁ የህዝብ መሰረተ ልማትና አገልግሎቶች በመንግሥት እንዲቀርቡ ሊደርግ ይችላል፡፡

- የምርትና አገልግሎት አምራች፥ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ትስስር ህጋዊ፥ ቀልጣፋ እና ተደራሽ የሚያደርግ አሰራር ይዘረጋል።
- ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተከልሎ የቆዩትን የገቢ፣ የወጪ፣ የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ሥራዎችን ለውጭ ባለሀብቶች ለመክፈት የተጀመረው ሪፎርም ተጠናክሮ ይቀጥላል።
- አምራቹንና ሸማቹን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል ከነፃ ገበያ ትይዩ የሆነ በሚታወቅ ህግና አሠራር የሚመራ አማራጭ የግብይት ሥርዓት ይዘርጋል። በተለይም የግብርና ምርት አምራቾችን ፍትሃዊ የዋጋ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የሚያስችል የማምረቻ ወጪ መሠረት ያደረገ ዝቅተኛ የአምራቾች መሸጫ ዋጋ ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡
- ሸማቹን ማህበረሰብ ከዋጋ ንረትና ተገቢ ካልሆኑ የገበያ ድርጊቶች ለመታደግ የሚያስችል በተመረጡ መሠረታዊ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ የትርፍ-ህዳግ ጨምሮ የአቅርቦትና የሥርጭት የቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል።
- ሸማቾች፣ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በገበያ ውስጥ የመደራደር አቅም እንዲኖራቸው በህብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁ ሁኔታዎች ይመቻቻል፣ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።
- የተሳለጠ የሀገር ውስጥ ግብይትና ሥርጭት እንዲኖር የሚያስችሉ ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት፣ የገበያ መሰረተ ልማትና የሎጅስቲክስ አቅርቦት ሥርዓት ይዘረጋል፣በዚህ ረገድ መንግሥት የግል ሴክተሩን ጥረትና ተሣትፎ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።
- በኢኮኖሚው ውስጥ የሚታየውን መዋቅራዊ የአቅርቦትና የእሴት ጭማሪ ክፍተቶችን ለማስተካከልና ቀጣይነት ያለው የሀገር ውስጥ ምርት አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ እንዲቻል በግብርናና በማንፋክቸሪንግ ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ አምራቾች ልዩ የፋይናንስና የቀረጥ ማበረታቻ እንዲሁም የመሠረተ ልማት ድጋፍ ይደረጋል፣ ከዚህ አንፃር ትርፍ አምራች አካባቢዎች የመንገድና የገበያ ትሥሥር እንዲኖራቸው ይሠራል።
- የንግዱ ዘርፍ ለሀገራዊ ዕድገትና ብልፅግና የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ከማስቻል አንፃር በአሁኑ ወቅት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የንግድ ሥራ ለመጀመርና ውጤታማ ሁኖ በመስኩ ለመቆየት ያለውን የንግድ ከባቢያዊ አመቺነት በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል መንግሥት ፈጣን የማሻሻያ እርምጃዎችን ይወስዳል።

ተገማችና ቀለል ያሉ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተና በቴክኖሎጂ የታገዘ፤ ግልፅነትና ተደራሽነት ያለው የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

- በሀገር ውስጥ ንግድ በኢ-መደበኛ መንገድ በስፋት እየተንቀሳቀሱ ያሉት ተዋናዮች ወደ መደበኛ ንግድ እንዲገቡ ለማድረግ የንግድ ሥራን ለመጀመር እና ለማከናወን ያለው አመቺነት የበለጠ ተደራሽና ቀላል እንዲሆን የማሻሻያ ሥራ ይሠራል፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው የታክስ ሥርዓት አነስተኛ ነጋዴዎችንና ጀማሪዎችን ወደ መደበኛ የንግድ አሠራር ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት በሚደግፍ አግባብ እንዲቃኝ ይደረጋል፡፡
- በንግድ ሥርዓቱ የሚሳተፉትን ተዋናይ ለማስፋት እና ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ የሚያስችል ግልፅና ፍትሃዊ አሰራር ያለው የአክሲዮን ንግድ ሥርዓት ይተገበራል፡፡
- በገበያ ውስጥ የሚፈጠሩ ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ተግባራትንና የግብይት ሰንሰለት በጥቂት ነጋዴዎች በሞኖፖል እንዳይያዝ ለመከላከል ሲባል የንግድ ሥራ ፈቃዶች ለተሠጠባቸው የስራ መስኮች ብቻ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የንግድ ሥራ ህጋዊነትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የድህረ ፈቃድ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትም በተጠናከረ አግባብ ይተገበራል፡፡
- መንግሥት ከግሉ ሴክተር ጋር በመቀናጀት ሸማቹ የሀገር ውስጥ ምርት የመሸመት፤ የመጠቀምና በሀገር ምርት የመኩራት ባህሉን ከፍ ለማድረግ ሰፋፊና ቀጣይነት ያላቸው የሀገር ውስጥ ምርት የማስተዋወቅ ሥራዎች ይሠራሉ፤ "የኢትዮጵያን ይግዙ" (Buy Ethiopian) እና "በኢትዮጵያ የተሠራ" (Made in Ethiopia) የመሳሰሉ መሪ ቃሎች በመጠቀም የሀገር ውስጥ ምርቶችን ለማስተዋወቅ ይሰራል፡፡

### 4.2 የገቢና ወጪ ንግድ አስተዳደር ማዕቀፍ

ሀገራዊ ኢንቨስትመንትን ለማሳብና ለማበረታታት፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች በዓለም ገበያ የሚኖራቸውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ጥራታቸው የተጠበቀና ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ ለማድረግና የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪነት ለመደገፍ የሚያስችል ግልፅነት ያለውና ፍትሃዊ የሆነ የወጪና ገቢ ንግድ አስተዳደር ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን መንግሥት በፅኑ ያምናል፡፡ ይህን ዓላማ ለማስፈፀም ጥቅም ላይ ከሚውሉት የገቢና የወጪ የንግድ አስተዳደር መሳሪያዎች መካከል የጉምሩክ ታሪፍ ወይም ቀረጥና ከቀረጥ ጋር የተያያዙ እርምጃዎች፣ ታሪፍ ያልሆኑ

እርምጃዎች፣ የተለያዩ የቁጥጥር ሥርዓቶች፣ ገደቦች እና ማበረታቻዎች ከሀገራዊ ፍላጎትና ጥቅም አንፃር በወጪና ገቢ ንግድ ተወዳዳሪነት ላይ የሚፈጥሩት ተፅእኖ እየተመዘነ መተግበር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

እነዚህ የገቢና የወጪ የንግድ አስተዳደር ሥርዓቶች በጥናት ላይ በመመሥረት በጥንቃቄ እና በአግባቡ ካልተቀረፁና ካልተመሩ ወደ ውጭ የመላክ አቅም እና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ፣ የሀገር ውስጥ ምርታማነትን ይጎዳሉ፣ ለተጠቃሚዎች በተለይም ለዝቅተኛ ገቢ ህብረተሰብ ፍትሃዊ ዋጋን የማያረጋግጡ እና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመከላከል እንዳይቻል ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ ከመጠን ያለፈ የታሪፍና ታሪፍ ያልሆኑ እርምጃዎች ሀገራዊ ኢንቨስትመንትን ጭምር ሊያዳክም እንደሚችል በመረዳት የሚከተሉት የፖሊሲ እርምጃዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- ሃገሪቱ በገባቻቸው የሁለትዮሽ፣ ቀጣናዊና ባለብዙ ወገን ስምምነቶችን ባከበረ መልኩ የማምረቻ ግብአቶች እና የፍጆታ ሸቀጦች ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ወደ ሀገር በማስገባት የአምራች ዘርፉንና የወጪ ንግዱን ተወዳዳሪነት የመደገፍ፥ ሸማቹ ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸምት የማስቻል፣ የሀገር ውስጥ ገበያውን በገፍ ከሚራገፍ ሸቀጥ የመከላከልና የመንግሥት ገቢን የማሳደግ አላማዎቹን በማጣጣምና ሚዛን ማስጠበቅ የሚያስችል የገቢ ዕቃዎች የግምሩክ ታሪፍና የክፍያ ተመን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ታሪፎችና ተመኖች በየጊዜው እየታዩ የሚከለሱ ይሆናል፡፡
- መንግሥት በተመረጡ ሴክተሮች የሀገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር ችሎታቸው እንዲያድግ እና እሴት በመጨመር ወደ ውጭ የመላክ አቅም እንዲፈጥሩ ለማበረታታት ልዩ የቀረጥ ተመን ይጠቀማል፡፡ ከውጭ በገፍ ከሚገቡ ምርቶችና ሸቀጦች ለመከላከል የሚያስችል የቀረጥ ተመን በመጠቀም ምክንያታዊ የሆነ ጥበቃና ድጋፍ ይደርጋል፡፡
- የውጪ ምርቶችን ተወዳዳሪነት ለመደገፍ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ይደርጋል፡፡ ነገር ግን ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸውና የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት የሚፈታተን ሁኔታ ሲያጋጥም በወጪ ምርቶች ላይ ምክንያታዊ የሆነ ቀረጥ ሊጣል ይችላል፡፡
- መንግሥት ግልጽ በሆነ አሰራር ላይ በመመስረት ለትምህርት፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለጤና እና በተለዩ የመንግስትና ህዝብና የበጎ አድራጎት አገልግሎት የሚውሉ ምርቶች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በተመረጡ

ሴክተሮች በተለይም ትርጉም ያለው እሴት ለሚጨምሩ ኢንቨስትመንቶች በውጤት ላይ የተመሰረተና ምክንያታዊ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

- በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ለተመረጡ የወጪ ምርቶችና አገልግሎቶች የኤክስፖርት ማበረታቻ ሥርዓት ተግባራዊ ይደርጋል ፡፡
- ሀገራችን ከገባቻቸውና በምትፈርማቸው የንግድ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ የወጪ ምርቶችን በዓይነትና በመጠን ለማሳደግ የሚያስችል ልዩና ነፃ የንግድ ቀጣና እና የኤክስፖርት ማቀነባበሪያና ማደራጃ ዞን ይደራጃል፡፡
- ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ የሚጣሉ ክልከላዎች እና የማስመጣት ፈቃዶች በግልጽ መስፈርቶች ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ መስፈርቶቹም የአካባቢ ጥበቃን፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ ጤና፣ የህዝብ ደህንነትና ሞራል እና ማህበራዊ ደህንነት እና ፍትሃዊ የሆነ የንግድ አሠራሮችን የሚያካትት ይሆናል፡፡
- የሀገር ውስጥ ዋጋ ለማረጋጋት፤ አምራቾችንና ሸማቹን ህብረተሰብ ከጉዳት ለመከላከል የሚያስችል መንግሥት በገቢ ምርቶች ላይ ኮታና ገደቦችን ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡
- መንግሥት የሀገር ውስጥ አምራቾች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የሀገር ውስጥ ምርቶች የገበያ እድሎችን ለማግኘት የሚያስችል የስራት ሀገር ደንቦችን ማዕቀፍ ያዘጋጃል፡፡
- ሀገራዊ አቅርቦትና ፍጆታን አደጋ ላይ የሚጥል ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እስካላጋጠመ ድረስ መንግሥት የወጪ ምርት መጠን የመገደብ ወይም ጨርሶ የመከልከል ፍላጎት አይኖረውም፡፡
- የማምረቻ ወጪን ለመቀነስና የምርቶችን የመሸጫ ዋጋ ተወዳዳሪ ለማድረግ ለግብዓትነት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎቸ ማቆያ የጉምሩክ መጋዘን አገልግሎት ሥርዓት በመዘርጋት የሚያጋጥመውን የሥራ ማስኬጃ ዕጥረት ለማቃለል ይሠራል፡፡

### 4.3የሸማቾች መብት ጥበቃ እና ፍትሃዊ ንግድ

በኢትዮጵያ ሸማቹን ማህብረተሰብ በሚመለከት ከኢ-ፍትሃዊ ግንኙነቶችና ተገቢ ካልሆኑ የንግድ አሰራሮች ለመጠበቅ ታስበው የተዘጋጁ ሕጎች፤ ደንቦች እና መመርያዎች ቢኖሩም በሚገባ ባለመተግበራቸው በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ከነዚህ ችግሮች መካከል የሸማቹን ማህበረሰብ ጤንነት፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበረሰባዊ እሴቶች የሚጎዱ ንግዶች እና አገልግሎቶች እየተበራከቱ

መሆናቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ችግሮቹ እየጨመሩ በመምጣታቸው ሸማቹ ማህበረሰብ ሀገር ውስጥ በሚሸምተው ምርት እና አገልግሎት እምነት እንዲያጣ ከመሆኑም በላይ ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ እንዲሆን አብቅቶታል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ አገራችን ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም አላገኘችም ፤ የዘርፉ ተዋንያንም ለተሻለ እድገት እና ብልፅግና ሊያበቁት አልቻሉም፡፡ በተቃራኒው የንግድ ዘርፉ በኢ-ፍትሃዊ አሰራር በመተብተቡ ለህገወጦች ምቹ አጋጣሚ በመፍጠሩ ህገ-ወጥ ንግዶች በዘርፉ እንዲስፋፉ፤ ኢ-ፍትሃዊ የንግድ እንቅስቃሴዎች እንዲበራከቱ ምክንያት ሆኖ ወደ ዘርፉ ሊገቡ የሚፈልጉ አዳዲስ የንግድ ተዋንያን ግለሰቦች እና ተቋማት ተስፋ እንዲቆርጡ ሰበብ ሆኗል፡፡

ስለሆነም መንግስት ይህንን የሸማቾች መብት ጥበቃ ዋነኛ የፖሊሲ ጉዳይ መዘጋጀቱ የሸማቾችን መብትና ጥበቃ ግንዛቤ በመፍጠር ሸማቹ በተደራጀ መልኩ ውጤታማ በሆነ መንገድ መብቱን ለመጠበቅ እንዲችል እና በገበያ ቦታ መተማመንን የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ ሸማቾች በበቂ መረጃ ላይ ተመስርተው የግብይት ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም የንግዱ ዘርፉ ተገማች እና ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበት ገበያ እንዲፈጥር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መንግስት የሀገር ምርት እና አገልግሎት ይበረታታ ዘንድ መስራት ካለበት ዋና ዋና ነገሮች መሃል በልዩ ሁኔታ የሀገር ውስጥ አምራቾችን ምርት በመንግስት ግዥ ውስጥ ቅድሚያ አግኝተው እንዲሸምቱ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ሲባል ከዚህ ቀደም በፖሊሲ ደረጃ ባለመቀመጡ በሀገር ደረጃ ወጥ አሰራር እንዳይኖር አድርጎታል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ምርት እና አገልግሎት በመንግስት ግዥ ውስጥ በሚገባ ቦታ ባለማግኘቱ ዜጎች በሃገራቸው ምርት እንዳይኮሩ፣ አምራቾች ከድካማቸው ተገቢውን ትርፍ አግኝተው ምርታቸውን እንዳያሳድጉ እና መንግስት ለውጭ ሀገር ግዥ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመሙላት ሲባል እና መንግስት፣ ሸማቹ እና የንግዱ ማህበረሰብ ከዘርፉ ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፡-

### 4.3.1 የሸማቾች መብት ጥበቃ

መንግስት ለዜጎቹ ምቹ የንግድ አካባቢን በመፍጠር እና ለአምራች ኢንተርፕራይዞች የማምረት እድሎችንና ድጋፍ በማመቻቸት ለሸማቾች ፊ የገበያ ምርጫ፣ ፍትሃዊ ዋጋ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርት አቅርቦትን በዘላቂነት በማረጋገጥ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል፡፡ መንግስት በሁሉም አይነት መንገድ የሸማቹን ጤና፣ ደህንነት እና አኮኖሚያዊ ጥቅም የማስጠበቅ ሃላፊነቶችን ተቀዳሚ ተግባሩ አድርጎ ይሰራል፡፡

- የሸማቾች መብት እና ጥቅም ለማስከበር፤ ኢ-ፍትሃዊ እና ተገቢ ያልሆነ የግብይት ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችል ግልፅ፣ ዘመኑን የዋጀና ሁሉን አቀፍ ጠንካራ የሸማቾች መብት ጥበቃ የህግ ማዕቀፍ እና አስፈፃሚ አካል ተሻሽሎ ይተገበራል፡፡
- መንግስተ ሸማቾች ስለሚሸምቱት ምርትና አገልግሎት በቂ መረጃ እና እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል በሀገር አቀፍ ደረጃ የግንዛቤ መፍጠሪያ ፕሮግራም ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡
- ሸማቾች በየደረጃው በማህበር ተደራጅተው ስለመብታቸውና ጥቅማቸው መሟገት እንዲችሉና በልማት እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ መሠረታዊና ሀገር አቀፍ የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፤
- የሸማቾችን ጥቅም እና ፍላጎት አደጋ ላይ የሚጥሉ የህግ ጥሰቶች እና አለመግባባቶች ሲከሰቱ የሚፈቱበትን ግልፅ አሰራር ያለው ችግሮችን በፍጥነት የሚፈታ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

### 4.3.2 ፍትሃዊ ንግድ ማስፈን

- መንግስት በሀገር ደረጃ ምርትና አገልግሎት ለሚያቀርበው ነጋዴ ፍትሃዊ የመወዳደርያ ከባቢ መፍጠር እና አዳዲስ ፈጠራዎችን በመጠቀም ምርት እና አገልግሎቱን የሚያሳድግበትና ውጤታማ የሚሆንበት አጋጣሚ እንዲያገኝ እድሎችን ያመቻቻል፡፡
- በሀገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ በሚካሄዱ የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሀገራችን ምርት እና አገልግሎት ተወዳዳሪ እና ተመራጭ እንዲሆን ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን የሚያበረታታ፣ ህገ- ወጥ የንግድ አካሄዶችን በሚገባ መከላከል እና ማቆም የሚያስችል ፍትሃዊ የንግድ ህጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡ ተግባራዊነታቸውንም የሚከታተል እና የሚያስፈፅም አሰራር ይዘረጋል፡፡

- ህጋዊ የንግድ ውድድሮችን የሚጎዳ ድርጊቶች ወይም አለመግባባቶች በተለይም ያልተገባ ክምችት በመያዝ የአቅርቦት እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ፣ እንዲሁም ሆን ተብሎ ህጋዊ ነጋዴዎችን ከገበያ ለማስወጣት የሚደረግ ህገ-ወጥ ድርጊት እንዳይፈጠር ይሰራል፡፡ ችግሩ ሲያጋጥም አፋጣኝ መፍትሄ ወይም ዳኝነት የሚሰጥ አሰራር ይተገበራል፡፡ በየደረጃው የንግድና ኢንቨስትመንት ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡

### 4.3.3 አዕምሯዊ ንብረት

- መንግሥት የብሔራዊ አዕምሯዊ ንብረት መብቶች ሕግ አፈፃፀምን በማጠናከር አዳዲስ ፈጠራዎችንና አሰራሮችን ያበረታታል፤ የአዕምሯዊ ንብረት መብትና ጥበቃን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአዕምሯዊ ንብረት ጋር የተያያዙ ተዛማጅነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ሰነዶችን፣ምርምርን እና ልማት ያከብራል ይደግፋል፡፡

### 4.4 ብዝሃ-ዘርፍ የወጪ ንግድ እና ተወዳዳሪነት

የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ትልም ዘላቂ፣ ሰፊ መሰረት ያለውና፤ የምርት አይነቶችና የመዳረሻ ገበያዎችን በማሳደግ የአፍሪካ የብልፅግና ሞዴል መሆን ነው፡፡ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ላለችው ሁለንተናዊ እድገት የወጪ ንግድ ዘርፍ እያበረከተ ያለው ሚና የበለጠ ጎልብቶ የሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ዘርፉ በርካታ መዋቅራዊና ያተገባበር ተግዳሮቶችና ማነቆዎች የሚስተዋሉበት በመሆኑ ለኢኮኖሚው እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከዘርፉ እምቅ አቅም አንጻር ዝቅተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ወደ ዉጪ የሚላኩ ምርቶችና አገልግሎቶች ስርጭትና ብዛት፣ የምርት አይነቶች እና የመዳረሻ አገሮች የወጪ ንግድ  ገበያ ብዛት ዉጫዊ ስጋት እና ተጋላጭነትን ይቀንሳል፡፡ ይህ በተለይ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የሚያደርገው አብዛኛዉ የወጪ ንግድ  የአየር ንብረት መለዋወጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ እንደ ቡና፣ ሰሊጥ እና ጫት ያሉ የግብርና ምርቶች ከሚመነጨዉ የዓለም አቀፍ የግብርና ምርቶች ዋጋ መዋዠቅ ምክንያት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ በርካታ ፈተናዎችን እና ስጋቶችን ይፈጥራል፡፡ የኢትዮጵያ ወጪ ንግድ ብዝሃነት የአቅርቦትን ችግር እና የፍላጎትን ውስንነት ችግር መፍታት አለበት፡፡

ከዚህ አንጻር የዘርፉን ነባራዊ ሁኔታ እና የሀገራችንን ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ፖሊሲን መሰረት ያደረገ የወጪ ንግድ ብዝሀነትና ተወዳዳሪነት የፖሊሲ አቅጣጫ መተግበር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ይህ የፖሊሲ አቅጣጫ መንግሥት በወጭ ንግድ መስክ ለሚተገብራቸው አጀንዳዎች እና

ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ግልጽ አቅጣጫዎቸን የሚያመላክት ነው። አቅጣጫው የተቀረፀው በአገራችን እየተገነባ ባለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሲሆን የግሉን ዘርፍ ዋነኛ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት ሚናውን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

በዚሁ መሰረት ያለብንን መዋቅራዊ እና ያተገባበር ተግዳሮቶቻችን በመፍታትና ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ፣ ወጪ ንግድን የማስፋፋት እና የወጪ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠን እና በመዳረሻ ገበያ ለማሳደግ እና የወጪ ንግድ እድገትን እውን ለማድረግ የሚከተሉት ቁልፍ እርምጃዎች ይተገበራሉ።

- የወጪ ንግድ ብዝኃነት በብዙ ታዳጊ ሀገራት ውስጥ ካለው የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በአዎንታዊ መልኩ ይዛመዳል። ኢትዮጵያ ለአብዛኞቹ የውጭ ገበያዎች ምርት የምታቀርብ ቢሆንም፣ ተመሳሳይ አቅም ካላቸው አገሮች በሚገኙ ገበያዎች ተወዳዳሪ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው። በመሆኑም መንግስት ምርታማነትን፣ የምርት መጠንን፣ ጥራትን እና እሴትን በመጨመር፤ አዳዲስ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን ወደ ወጪ ንግድ ቋት በማስገባት ዓለም አቀፍ የገበያ እድሎችን አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል አቅጣጫ ይከተላል።
- በአገልግሎት የወጪ ንግድ ዘርፍ ተነፃፃሪ ተወዳዳሪነት ባላቸው እንደ ቱሪዝም፤ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ፣ ሙያዊ አገልግልቶች እና በኤሌክትሪክ ኤክስፖርት ዘርፎች/ምርቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል።
- የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ ስርዓቶችን እና መሠረተ ልማቶችን በመዘርጋት አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለማሳደግና በነባሮቹ መዳረሻዎቻችን የገበያ ድርሻችንን ለማሳደግ የሚያስችሉ አካሄዶች በመከተል እና የላኪዎችን አቅም በማሳደግ ላኪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና በገበያ ላይ መሰረታቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲገነቡ ይሰራል።
- ለኢንተርፕራይዞች የተለያዩ ድጋፎችን እና ድጎማዎችን የሚሰጥ የወጪ ንግድ እድገት ፋሲሊቲ (Export Growth Facility) በማቋቋም ተወዳደሪነታቸውን የማሳደግ ስራዎች ይሰራሉ።
- በገዥ ፍላጎቶች ላይ ያተኮረ የወጭ ምርቶች ማምረት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሳካ ኤክስፖርት-መር ልማት ወሳኝ አንቀሳቃሽ በመሆኑ ገዥ-ተኮር (buyer-led) አካሄድ

በመከተል ሊገኙ የሚችሉ ገበያዎችን በመለየት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብና ምርታማነትን እና የምርት ብዝሃነትን ለማሳደግ ይሰራል፡፡

- የግል ዘርፍ ተሳትፎን ለማፋጠን ማበረታቻ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ተሳትፎን በማጠናከር ትልልቅና ስትራቴጂካዊ ባለሀብቶችን በቁልፍ ንዑሳን ዘርፎች ከመሳብ ጋር በትይዩ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ንዑስ ዘርፎች ምቹና አስቻይ ሥነ-ምህዳር ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በቁልፍነት በተመረጡ ዘርፎችና ንኡስ ዘርፎች (ለምሳሌ ቶዳና ጨርቃ ጨርቅ) ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠርና ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ያደረገችው ጥረት ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንቨስትመንቱን ለመሳብ ከተሰራው ስራ አኳያ ሲወዳደር ስኬታማ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ አሁን ባለንበት የዕድገት ምዕራፍ የሀገሪቱ ስነ ምህዳር ከኢንዱስትሪው እድገት ጋር አብሮ መጓዝ እንዲችል ቁልፍ በሆኑ ንዑስ ዘርፎች ላይ ስትራቴጂክ ኢንቨስትመንትን ከመፈለግ ጎን ለጎን አስቻይ ምህዳር የመፍጠርና የማልማት ስራ ይሰራል፡፡
- በዓለም ገበያ ተፈላጊ የሆኑና ኢትዮጵያ የማምረት አቅም ከፍተኛ የሆኑ፣ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስገኙ የሚችሉ ምርቶች/አገልግሎቶች እንዲሁም ብዙ እያመረትናቸው ባይሆንም የተለየ የጥራት ባህሪ ያላቸውን እና በዓለም ገበያ ተፈላጊ የሆኑትንም ለይቶ ብራንድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ኤክስፖርትን በብቃት ማስተዋወቅ፤በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ቁልፍ በሆኑ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ላይ የገዥዎችንና ባለሀብቶችን ግንዛቤ በማስፋት፣ ለሀገሪቱና ለቁልፍ ሴክተሮች ተጨማሪ ኢንቨስተመንት መሳብ በትኩረት ይሰራል፡፡
- ውጤታማ ቅንጅትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ የሆኑ ሥርዓቶችንና ሂደቶችን ያካተተ ተያያዥ ድጋፎችን ለማቅረብ የመንግስትን ተቋማዊ አቅም በማሳደግ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እና የዓለም ገበያ የጥራት መስፈርቶችን ለማሟላት በሚያስችል መልኩ የተቀናጀ፣ ወጥ እና ግልጽ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ ያለው የወጪ ንግድ አስተዳደር መዋቅር እና ማዕቀፍ እንዲሁም ኤክስፖርትን ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመገንባት የወጪ ንግድ አፈጻጸምን የሚያሳልጡ ቅንጅታዊ አሰራሮች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

- የተመረጡ የወጪ ምርቶች ከፍተኛ የማምረት አቅም ያላቸውን አካባቢዎች መሰረት ያደረገ **የወጪ ንግድ ምርቶች ኮሪደር ልማት** በተደራጀ እና በተቀናጀ ሁኔታ ይሰራል፡፡ በሀገራችን ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ኮሪደር ልማት የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ አቅም ለማጠናከር ያለመ ዘርፈ ብዙ ስትራቴጂን ያካትታል፡፡ ይህም በተወሰኑ ጂኦግራፊያዊ ኮሪደሮች ውስጥ የተወሰኑ ምርቶችን ማስተዋወቅ እና መሠረተ ልማትን ማጎልበትን ያካትታል፡፡ በተለዩት ኮሪደሮች ላይ ያሉትን የምርቶችን ፍሰት ለማሳለጥ እና ተወዳዳሪነትን የሚያሳድጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች በመገንባት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር እና የወደፊት የንግድ ልውውጥ ዕድገትን ማስተናገድ የሚችል ስራዎች ይሰራሉ፡፡
- የሀገሪቱ ወጪ ንግድ ሥርዓት ያለበትን የተበታተነ እና ያልተቀናጀ አሰራርን የሚፈታ ወጥ በሆነ እሳቤና አመራር እንዲኖረው የሚያስችል አደረጃጀት ተፈጥሮ ይመራል፡፡

### 4.5 በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር ዉስጥ መሳተፍ

ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት የዓለም ምርት ሂደት በተለያዩ አገሮች በከፍተኛ ደረጃ የተበታተነ እና የተሰራጨ ነው፡፡ መሪ በሆነው አምራች ድርጅቶች አማካኝነት የምርት ስራ በርካታ ድርጅቶች የሚሳተፍበት ሲሆን በድርጅቶች መካከል ያለዉን ትብብር የሚያሳልጡ የተለያዩ የኮንትራት እና የአጋርነት አሰራሮች አሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ድርጅቶች በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (global production network (GPN)) ዉስጥ መሳተፋቸው፤ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስገኙ የሚችሉ እሴት የተጨመረበት የወጪ ምርት ለማቅረብ፣ ምርታማ የሆነ ኢንቨስትመንት እንዲኖር፣ ደረጃውን የጠበቀ ምርት ለማምረትና አስተማማኝ ገበያ የማግኘት፣ እና አካታችና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣ የማድረግ አቅም ይፈጥራል፡፡ የተሳካ በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር ዉስጥ ተሳትፎ ለማድረግ የንግድ ፖሊሲ የሀገሪቱን ንግድና ኢኮኖሚ ከዓለም አቀፍ ምርት ሂደት ጋር የሚኖረዉን ትስስር ለማሳለጥ ያስችላል፡፡ ስለሆነም የሀገራችን አምራቾች በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር ውስጥ የላቀ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

- የዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (GPN) ፍላጎትና ሀገራዊ የአቅም ትንተና ላይ የተመሰረተ ጥናት በማካሄድ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን ዘርፎች መለየት እና ተሳትፎ ለማድረግ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች እንዱስትሪ ዉስጥ ያለዉን አጠቃላይ የምርት ሂደት ከጥሬ ቆዳ ጀምሮ ተዘጋጅቶ የተሰራ ቆዳ፣ ያለቀለት ቆዳ፣ የቆዳ ክፍሎች (leather components) እና የቆዳ ውጤቶችን እስከ

መጨረሻው ድረስ በመለየት ሀገሪቱ በምን ላይ መሳተፍ እንደምትችል ይለያል። ቅድሚያ በሚሰጣቸዉ ዘርፎች አጠቃላይ የምርት ሂደቱን መተንተን፣ ደንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎች የሚያመርቷቸውን ምርቶች መሰረት ያደረገ ትንተና በማድረግ እና የሀገር ዉስጥ ኩባንያዎች በምረት ትስስር ላይ ዉጤታማ በሆነ መንገድ የሚሳተፉባቸዉ ዘርፎች በመለየት ይሰራል።

- የዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (GPN) ተሳትፎን ለማሳለጥ ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የገበያ ተደራሽነትን ማሻሻል እና ከዋና ዋና የንግድ አጋሮች ጋር ያለዉን የኢኮኖሚ ትስስር ለማጠናከር ይሰራል። የማምረት ትስስር የተመሰረተው በድንበር ተሻጋሪ የንግድ ፍሰት ስለሆነ የንግድና የኢንቨሽትመንት መሰናክሎችን የሚያስወግድ የንግድ ስምምነቶችን ድረግ እና የትብብር ማዕቀፎችን የማጠናከር ስራ ይሰራል።
- የዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (GPN) ዉስጥ ለመሳተፍ ጥራት ያለው ምርት ማምረት ያስፈልጋል። ድርጅቶች ጥራት ያለዉ ምርት ለማምረት ከውጪ የሚገቡ ጥራት ያላቸዉ ግብዓቶችን ማግኘት አስፈላጊ ስለሆነ በዚህ ትስስር ውስጥ ላሉ አምራቾች የሚጠቀሙባቸው የምርት ግብአቶች ወደ ሀገር ዉስጥ በተወዳዳሪ ዋጋ የሚገቡበት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የማበረታቻ ሥርዓት ይተገበራል።
- በኢትዮጵያ የልማት ዕቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች አንዱ በኢኮኖሚ ዉስጥ የግሉን ዘርፍ በላቀ ሁኔታ ማሳደግ ስለሆነ የግሉ ዘርፍ አመራር ብቃት ለማሳደግ ጠንካራ የመንግሰት እና የግል አጋርነት በመፍጠር በገበያ የሚመራ ኢኮኖሚ መገንባት ነው። ስለሆነም የዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (GPN) የሚመራ ልማት ስኬታማ እንዲሆን የመንግሰት እና የግል አጋርነት (PPP) እና የትብብር ኢንቨስትመንት ማጠናከር እንዲሁም የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አቅም በመጨመር ምርትን ለማሳደግ ይሰራል።
- የዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (GPN) ውስጥ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጠንካራ ትስስር እንዲፈጥሩ ለአንስተኛ እና ለመካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የአቅም ግንባታ እና ፋይናንስ ድጋፍ ይደረጋል። ድርጅቶች በዘላቂነት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅራቢ ልማት ፕሮግራም (supplier development programs (SDPs)) በማመቻቸት ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በማድረግ የምርቶችን ጥራት እና ደረጃዎች እንዲያሻሽሉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የንግድ ድርጅቶች አዳዲስ ፈጠራዎችን እንዲያወጡ እና ከውጪ ድርጅቶች ጋር ሽርክና ለመፍጠር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራ በተደራጀ ሁኔታ ይሰራል።

- የአግልግሎት ንግድ የዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (GPN) ውስጥ ለመሳተፍ አስፈላጊ የሚያደረገው በኩባንያዎች መካከል የሚኖረውን የትስስር ስራዎች ብቻ ሳይሆን ድርጅቶች የሚያቀርቧቸውን ምርቶች ተፈላጊነት እንዲያሳድግ ያደርጋል። ስለሆነም በተመረጡ እና ሀገራዊ አንፃራዊ ጠቀሜታ ባላቸው የአገልግሎት ንግድ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ንግድ ሰንሰለት ውስጥ የሚሳተፉበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።

### 4.6 ከባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ግንኙነት እና ኢኮኖሚያዊ ውህደት

ኢትዮጵያ ታዳጊ እና እምቅ ሀብት ያላት ሀገር እንደመሆኗ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት፣ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት እና ድህነትን ለመቅረፍ ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂ እና ሁለገብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በዓለም አቀፍ የንግድ መድረክ ውስጥ መሳተፍ እና የንግድ ግንኙነት መፍጠር አስፈላጊ ነው። መንግስት ግልጽና ፍትሃዊ የንግድ ግንኙነት በሰጥቶ መቀበል መርህ ከዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር ለመዋሃድ፣ የወጪ ንግድን ለማስተዋወቅ፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና የስራ እድልን ከመፍጠር አንፃር በባለብዙ ወገን፣ አህጉራዊ፣ የሁለትዮሽ እና የልዩ ተጠቃሚ የንግድ ስምምነቶችን ላይ ያላት ተሳትፎ ዝቅተኛ በመሆኑ ጥቅሞቿን ለማስጠበቅ የገበያ እድሎችን ለማስፋት የተደረጉ ጥረቶች በቂ ናቸው ማለት አይቻልም።

በዓለም ገበያ ውድድር ትርጉም ያለው ተፅዕኖ መፍጠር የሚያስችል ደረጃ ላይ እስከሚደረስ ድረስ ተገቢውን ሚና ለመጫወትና ድርሻችንን ለማግኘት የሚያስችል ፍትሃዊና ውጤታማ ድርድር የማድረግ አስፈላጊነት የዚህ ፖሊሲ ወሳኝ ጉዳይ እንዲሆን በሰነዱ ተካቷል። የኢትዮጵ የንግድ ግንኙነት እና ውህደት ፖሊሲ የሀገሪቱን ዘላቂ ልማት፣ኢንዱስትሪላይዜሽን እና ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜ ቃልኪዳን ለገባችባቸው፣ የመግባቢያ ስምምነት ለተፈራረመችባቸው እንዲሁም ንቁ ተሳትፎ ለምታካሂድባቸው የባለብዙ ወገን እና ክልላዊ ትብብር ሰፊ ግቦች ጋር እንዲተሳሰሩና እንዲስማሙ ይደርጋል።

የኢትዮጵያን ምርቶችና አገልግሎቶች የገበያ ተደራሽነት በማስፋት የወጪ ንግድ ብዝሃነትን በማጎልበት ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማሳደግ ያስችላል። ቀጣናዊ እና ክልላዊ ውህደትን በተለይም በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) እና ክልላዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች የአፍሪካን የዉስጥ ንግድ ለማስፋፋት ያግዛል። ዓለም አቀፋዊ፤ ቀጣናዊ እና ክልላዊ የአቅርቦት ሰንሰለቶችን ለማጠናከር እና የጋራ እድገትን ያበረታታል፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማሳደግ እና ኢንዱስትሪዎችን ዓለም አቀፍ

ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ድጋፍ በማድረግ የኢትዮጵያን የንግድ ተወዳዳሪነት ያሳድጋል እንዲሁም የቀረጥ ሆነ ከቀረጥ ውጪ ያሉ የንግድ መሰናክሎችን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ አስፈላጊ ስለሆነ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጧል፡፡

- የሁለትዮሽ፣ ቀጣናዊ እና ባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች ማዕቀፍ ውስጥ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ እና ሌሎች ሀገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፎች ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡
- የተጀመረውን የአባልነት የድርድር ሂደት በማፋጠን ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አባል በመሆን ከዓለም አቀፍ የንግድ ህግጋት፣ የገበያ መዳረሻ ዕድሎች እና የክርክር አፈታት ዘዴዎች ተጠቃሚ እንድትሆን ይሰራል፡፡
- በንግድ ድርድር ላይ ለሚሳተፉ እና የንግድ ግዴታዎችን መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚሰሩ የተለያዩ የመንግስት እና ባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፡፡
- የጉምሩክ አሠራሮችን ለማቀላጠፍ፣ የንግድ ወጪን ለመቀነስ እና የድንበር ትራንዚት ቅልጥፍናን ለማሻሻል፣ የንፅህና እና የፋይቶ ሳኒተሪ (SPS)፣ የንግድ እንቅፋቶች፣ (TBT) ወዘተ በባለብዙ ወገን ንግድ የሚፈረሙ ስምምነቶች እንዲተገበሩ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) ስምምነት ሙሉ በሙሉ ይተገበራል፡፡
- ምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ)፣ የበይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ)፣ በብሪክስ ማዕቀፍ እና ሌሎች ቀጣናዊ የንግድ ስምምነቶች እንዲጠናከር ይሰራል፡፡
- ለኢትዮጵያ የወጪ ንግድ አዳዲስ ገበያዎችን ለመክፈት እና ነባር ገበያዎችን ለማስፋት፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማሳደግ ከዋና ዋና የንግድ አጋሮች ጋር የሁለትዮሽ ስምምነቶች በሰፊው ይሰራል፡፡
- በሁለትዮሽ ንግድ ስምምነት ውስጥ የኢትዮጵያን ነጋዴዎች እና ኢንዱስትሪዎች ኢፍትሃዊ ከሆኑ ተግባራት ለመጠበቅ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚረዱ ሥርዓቶች ይዘረጋል ተጠናክሮም ይተገበራል፡፡

- ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚደረግ የድንበር ላይ ንግድ ለቀጣናዊ ኢኮኖሚያዊ ውህደት፣ በተለይም በድንበር አካባቢ ነዋሪዎች ማህበራዊ ትስስር እና ለቀጣናው ሰላምና ደህንነት ወሳኝ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም የደንበር ላይ ንግድን በህጋዊ መንገድ እንዲመራ፤ መደበኛ ያልሆነ የንግድ እንቅስቃሴን ለመቀነስ እና የድንበር ማህበረሰቦችን መተዳደሪያ እድሎች ለማሳደግ እንዲሁም የብሄራዊ ደህንነት እና የቁጥጥር ደረጃዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የድንበር ላይ ንግድ ኮንትሮባንድ እና ህገ ወጥነትን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ እንዲተገበር ቀልጣፋና ግልጽ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

### 4.7 የገቢና ወጪ ንግድ ማሳለጥ

የንግድ ማሳለጥ ማለት የቴክኒክ እና የህግ ሂደቶችን ማቅለልና ምቹ ማድረግ፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ልውውጥን በአቅርቦት ሰንሰለት ተዋናዮች ዙሪያ ማስፈን፣ የንግድ ሰነዶችን ከንግድ አጋሮች ጋር ማውሃድና ማቅለል፣ በክፍያዎች ላይ ግልጸኝነትን ማስፈን እንዲሁም በህጎችና መመሪያዎች ላይ ግልጽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ የሀገራችን የቴክኒክ እና የህግ ሂደቶች በርካታ ውጣ ውረድ ያለው፣ ግልጽነት የጎደላቸው እና ለሙስና የተጋለጡ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሂደቶቹ የመረጃ እጥረት እና የመሠረተ ልማት እጥረት ስላለባቸው ችግሩን አባብሶታል፡፡

አስተማማኝ የትራንስፖርትና የሎጀስቲክስ ዘርፍ ልማት እና የንግድና ኢንቨስትመንት ማሳለጥ ስራዎች ለወጪና ገቢ ንግድ መሳለጥ ወሳኝ ናቸው፡፡ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ የሆነ የሎጀስቲክስ ዘርፍ የወጪ እና ገቢ ንግድ ላይ የተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብን ጨምሮ አጠቃላይ የግሉን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ለማሻሻል  የሚረዳ ነው፡፡ እንዲሁም የወጪና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴን ከማሳለጥ አንፃር የጉምሩክ አገልግሎት ቁልፍ ሚና ይጫዎታል፡፡ የሀገራችን ሎጀስቲክስ ዘርፍ በሚገባ ያላደገ መሆኑ እና ደካማ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩ፣ በድንበሮች ላይ የሚደረጉ ፍተሻዎች እና በባህርና በደረቅ ወደቦች የሚከናወኑ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓቶች ቅልጥፍና የሚጎድላቸው መሆኑ በዓለም አቀፍ ንግድ ላይ የሚሳተፉ የንግድ ተዋናዮች ላይ የንግድ ወጪዎችን የሚጨምር ሲሆን በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ ያላቸውን ተወዳዳሪነታቸውንም  ይቀንሳል፡፡  እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ  እና አዳዲስ አሰራሮችን በመተግበር ያሉትን ወስንነቶች እና በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ ያሉትን የትብብር ጉድለቶች መቅረፍ አስፈላጊ ነው፡፡

እንዲሁም የጥራት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች እና ሸቀጦች ግብይት እና ስርጭት በሰዎች፣ በእንስሳት እና በእፅዋት ጤና እና ደህንነት ላይ አደጋ ከማስከተልም በላይ በገቢና ወጪ ንግድ ፍሰት ላይ ብሎም በሀገር ኢኮኖሚ እና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድር ተስተውሏል፡፡

በተጨማሪም የንግድ ወጪው በተነጻጻሪነት ከፍተኛ በሚሆንባቸው የአነስተኛ፣ የጥቃቅን እና የመካከለኛ ደረጃ ባላቸው ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፅዕኖው የጎላ ነው፡፡ የንግድ ማሳላጥ በተለይም በቀላሉ የሚበላሹ የግብርና ምርቶች ለሚያመርቱ አካላት ጊዜ በጣም ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት መስጠት ይገባዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የተዘረዘሩትን የንግድ ማሳለጥ ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስችል የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

- ኢንቨስትመንትን፣ ፈጠራን እና የአሰራር ቅልጠፍናን የሚያበረታታ የፋይናንስ ምህዳር በመፍጠር የኢኮኖሚ እድገትን እና የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ዘላቂነቱ የተረጋገጠ ጠንካራና ውጤታማ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሴክተር ይገነባል፡፡
- የግሉ ዘርፍ በትራንስፖርት እና ሎጆስቲክ ዘርፍ እንዲሳተፍ እና ተወዳዳሪና አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲያመጣ ይበረታታል፡፡
- የባህር ትራንስፖርት ዘርፉን እና መልቲሞዳል የትራንስፖርት ዘርፉን በማዘመን የአቅርቦት ሰንሰለቱን በማሳጠር በጊዜና በወጪ ረገድ ተጠቃሚ ለመሆን የሚረዳ አሰራር ይዘረጋል፡፡
- የንግድ ቀጣናውን ግንኙነት የሚያጠናክር፣ ንግድን የሚያሳልጥ፣ የኢኮኖሚ እድገቱን የሚያረጋግጥ እና ደረጃውን የጠበቀ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሥርዓት ይገነባል፡፡ ይኼንንም ለማሳካት መንግስት የመሰርተ ልማት ግንባታን በቁልፍ የትራንዚት ኮሪዶሮች ላይ፣ በደረቅ ወደቦች፣ በካርጎ አያያዝ እና በትራንስፖርት እንዲሁም በባቡር መንገዶች ላይ ይሰራል፡፡
- የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለህብቶችን በማቀናጀት ዘመኑን የዋጀ የቴክኖሎጂ አና የአሰራር ሥርዓት በማስፈን በቀጣናው ተወዳዳሪ የሆነ የትራንስፖርት እና የሎጂስቲክስ አገልግሎት እንዲገነባ ይደረጋል፡፡
- ሎጂስቲክን ለማሳልጥ የሚያስፈልጉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በማድረግ ከዓለም አቀፍ የሎጂስቲክ ማዕከላት (hub) ጋር ስትራቴጂክ ግንኙነት ይመሰርታል፡፡

- ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የቴክኒክ እና የአቅም ግንባታ ድጋፎች በመጠቀም የጉምሩክ ክሊራንስ መሰረተ ልማቶችን መገንባት እና የማስፋፊያ ስራዎች ይሰራል፡፡
- ወቅቱን እና አውዱን መሰረት ያደረገ የህግ ማዕቀፍ ማሻሻል፣ የጉምሩክ የአሰራር ሂደቶችን ማሻሻል፣ የደረጃዎች ቅንጅት፤ የአንድ መስኮት አገልግሎትን መተግበር፤ እንዲሁም በቀጣይ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በውስን የባህር ወደቦች ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቅረፍ የተለያዩ የንግድ መስመሮችን በመጠቀም ሀገራዊ የመደራደር አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡
- በሁሉም የንግድ ማሳለጥ ስራዎች የዲጂታል ቴክኖሎጂን በማስፋፋት የተሳለጠ እና ግልፅ አሰራርን በማስፈን በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ስራዎችን ይሰራል፡፡
- የተሳለጠ እና ያልተቆራረጠ ድንበር ተሻጋሪ የምርት እና የሸቀጦች ዝውውርን የሚያረጋገጥ፣ ጊዜን የሚቀንስ፣ የትራንዚት እና የሎጂስቲክ ሴክተሩን ቅልጥፍና የሚያረጋግጥ ድጋፍ ይደረጋል፤ ይኼም የጉምሩክ አሰራር ሂደቶችን በማዋሃድ (Harmonization) የኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ ሥርዓት በመተግባር፣ በየኬላዎች ላይ ያለውን መሰረት ልማት በማዘመን፣ የስጋት ስራ አመራር ሥርዓት በመተግበር ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው ምርት እና ሸቀጦች ላይ የኢንስፔክሽን ስራውን በማጠናከር እንዲሁም የገቢ ፈቃድን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት እንዲሆን በማድረግ ይሰራል፡፡
- በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እንዲሁም በቀጣናዊ የንግድ ስምምነቶች ላይ ያለውን ተሳትፎ በማጠናከር የመረጃ ልውውጡን በማሳደግ ዓለማቀፋዊ ተደራሽነት (connectivity) በመጨመር፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመደገፍ፣ ዘላቂነቱ የተረጋገጠ የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ ይሰራል፡፡
- የገቢና ወጪ ንግዱን የተሳለጠና ጠንካራ ለማድረግ መንግስት ጥራትን፣ ደህንነትን እና የዓለም አቀፍ ደርጃዎችን መተግበርን ያስቀደመ ስርአተ-ምህዳር (Eco-System) በመዘርጋት ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት እና የኢኮኖሚ እድገት ይገነባል፡፡ ደረጃዎችን እና የቴክኒክ ደንቦችን ከዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር በማቀናጀት ስጋት ትንተና ላይ መሰረት ያደርገ ውጤታማ የኢንስፔክሽን እና የጥራት ማረጋጋጥ ስራ ይሰራል፡፡

- ንግድን እና ጥራትን ለማሳለጥ በክፍለ አህጉራዊ፣ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደርጉ ጅማሮዎች (Initiative) በመያዝ እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር እና ከንግድ አጋሮች ጋር በመተባበር የቴክኒክ ደንቦችን እና የደረጃዎችን ወጥነት የማስተካካል (Harmonization) ስራ ይሰራል፡፡
- ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የጥራት መሰረተ ልማት በመገንባት የሀገሪቱ ምርት እና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ያላቸው ተቀባይነት እንዲያድግ እና ኤክስፖርት የሚያደርጉ ኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት ይሰራል፡፡ የጥራት ፍተሻ የሚያደርጉ ፋሲሊቲዎችን ያለማል ያጠናክራል፣ በዚህም ጥራትና ደህንነትን በማስጠበቅ ሸማቾችን ይጠብቃል፣ እንዲሁም ምርቶች ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

### 4.8 የገበያ መሰረተ ልማት ማስፋፋትና ማዘመን

የሀገራችን ንግድ ሥርዓት ስብራት ከሆኑት ችግሮች መካከል አምራችና ሸማቹን በቀጥታ የሚያገናኙ ምቹና ዘመናዊ የግብይት መሰረተ ልማት አለመሟላት አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ምርትና አገልግሎት በወቅቱ እና ጥራቱን ጠብቀው ሊደርሱበት የሚችሉበት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሥርዓት፣ ሸማቹ ምርትና አገልግሎት በሚፈልግበት ጊዜና መጠን በቅርብ ሊያገኝ የሚችልበት ምቹ የገበያ ቦታ፣ ምርቶች ሳይበላሹ የሚቆዩበት ምቹ የማከማቻ መሰረተ ልማት፣ ሸማቹ በቀላሉ የገበያ መረጃ የሚያገኝበት ዘመናዊ ቴክኖሎጂና አሰራር እንዲሁም ሻጩና ሸማቹ ቦታ ሳይገድባቸው ግብይት የሚፈፅሙበት የመገበያያ፣ የገንዘብ መክፈያና የማንንዣ ቴክኖሎጂና አሰራር የገበያ መሰረተ ልማት ከሚያካትታቸው ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ስለሆነም እነዚህን የገበያ መሰረተ ልማቶች ሀገራችን ባላት አቅም እና ቅድሚያ በሚሰጣቸው ላይ በማተኮር እንዲሟሉ በማድረግ የተሳለጠ፣ምቹና ዘመናዊ የንግድ ከባቢ በመፍጠር የሀገራችን ብልፅግና እውን ለማድረግ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

- የምርት አቅርቦትና ትስስርን የሚያጠናክሩ እና አምራቹንና ሸማቹን በቅርበት የሚያገናኙ መሰረተ ልማት የተሟላላቸው ምቹና ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት በከተሞችና ሸማች እና ምርት በብዛት በሚገኝባቸው አካባቢዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

- በየደረጃው ባለው የሀገር ውስጥና የወጪ ምርት ግብይት ሰንሰለት በሚገነቡት ምቹና ዘመናዊ የገበያ መሰረተ-ልማት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ እና ከመንግስት ጋር የሚኖረውን አጋርነትና ትብብር በሚያጠናክር መልኩ ይሰራል፡፡
- የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ማኑፌክቸሪንግ ሂደትን መለወጥ ብቻ ሳይሆን የእቃዎች እና አገልግሎቶችን ግብይት ክፍያ ሥርዓትንም ይቀይራል፡፡ በዚህም የተነሳ የወደፊት የዓለም ንግድ ማዕቀፍ በዲጂታል ንግድና ኢ-ኮሜርስ (e-comerce) ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያድርበት መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ የዲጂታል ንግድ ጽንሰ ሀሳብ የእቃዎች እና አገልግሎቶች በዲጃታል መንገድ ንግድ ማከናወን በሸማቾች፣ በድርጅቶች እና በመንግስታት መካከል የምርት ልውውጥ እንዲከናወን የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም መካከል እቃዎችና አገልግሎቶችን በዲጂታል ትእዛዝ መስጠት ድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (e-comerce) እና እቃዎችና አገልግሎቶችን በዲጂታል መንገድ ለሸማቹ ማድረስ (አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢንተርኔት ወይም በሌሎች መረቦች ማድረስን) ያካትታል፡፡ ስለሆነም የሀገራችን ተቋማት በሰፊ ገበያ ውስጥ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በዝቅተኛ ዋጋ እና በምቹ ሁኔታ በዲጂታል የተሳሰረ ዓለም አቀፍ ገበያ መግዛት እና መሸጥ የሚያስችል አመቺ የሆነ የዲጅታል ንግድ ሥርዓት እና ምቹ መሰረተ ልማት ለማሟላት ይሰራል፡፡
- የዲጅታል ንግድ አቅም ግንባታ እና ከሚኖረው የቴክኖሎጂው እድገት ጋር አብሮ የሚዘምን እና የተዋናዩን ህጋዊነት እና መብት የሚያረጋግጥ የቁጥጥር ሥርዓት የመገንባት ስራ ይሰራል፡፡
- የሁለትዮሽ፣ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ስምምነቶች ውስጥ ኢ-ኮሜርስ እና የዲጂታል ንግድ ድንጋጌዎችን በማካተት ሀገራችን አስተማማኝ የሆነ እና የበለጠ የገበያ ድርሻ እንዲኖራት እና የመረጃ ልውውጥ ፍሰት እንዲቀላጠፍ ይሰራል፡፡
- የጉምሩክ አገልግሎቶች፣ ሰነዶች፣ ድንበር ተሻጋሪነት፣ የኤሌክትሮኒክስ ማመልከቻ እና የገቢና ወጪ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥ መዘመን እና ዲጂታላይዝ መሆን የንግድ ዘርፍ ተወዳዳሪ እና ተገማችነት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

### 4.9 ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች

በዚህ የንግድ ፖሊሲ ሰነድ ውስጥ በባለ-ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ከንግድ ሥርዓቱ ጋር የሚገናኙ ሀገራችን የተቀበለቻቸውን የዓለም አቀፍ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ለማክበር፣ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመደገፍ፣ ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳትፏቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሀገራችን የምትከተለውን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት የሚያፋጥን የአየር ንብረት ጥበቃ ስራዎችን በሁሉም የፖሊሲ ጉዳዮች በማካተት እንዲፈፀሙ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

#### *4.9.1 ስርዓተ ጾታ*

በንግድ ፖሊሲው ውስጥ የፆታ እኩልነትን ማሻሻል ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገትን በማስመዝገብ ሀገራዊ ስትራቴጂክ የልማት ግቦችን (Goal 5 on Equality) ለማሳካት ያስችላል፡፡ ሀገራችን ከጾታ እኩልነት እና ከሴቶች እኩልነት እና መብት ጋር የተያያዙ በርካታ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያፀደቀች ሲሆን እነዚህን መርሆች በበርካታ የሀገር ውስጥ የዘርፍ ፖሊሲዎች ውስጥ በመርህ ተካተው በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡

ንግድና የሴቶች እኩልነትን በማስተሳሰር ኢትዮጵያ እኤአ በ2017 በተደረገው የዓለም ንግድ ድርጅት የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ የሴቶችን ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የጋራ ውሳኔ ተቀብላለች ፡፡ በውሳኔው ላይ ሀገሮች የተስማሙት በሴቶች ላይ በመንግስት ግዥ የሚያጋጥሟቸውን የንግድ እንቅፋቶችን በተሻለ መንገድ ለመቅረፍ የሚያስችሉ መንገዶችን በመፈለግ እና የንግድ ስራ ፋይናንስ ለማገዝ እንዲሁም ተሳትፏቸውን ለማጠናከር ተስማምተዋል፡፡ ስለሆነም መንግስት የሚከተለውን የፖሊሲ አቅጣጫ ይከተላል፡፡

- የንግድ ሥርዓቱ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትና አቅም በማጎልበት የጎላ ሚና እንዲኖረው፤ እንዲሁም ሴቶች እንደ ሥራ ፈጣሪነት፣ ተቀጣሪነት እና ሸማች በመሆናቸው ተፅእኖ እንዳይደርስባቸው ይሰራል፡፡
- ሴቶች ሥራ ፈጣሪ በሆኑበት ዘርፍ ላይ በሴቶች በሚመሩ የንግድ ዘርፎች እና ምርቶች ላይ የተሻለ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በተመረጡ የንግድ ዘርፎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- ሀገሪቱ የምታደርጋቸው የንግድ ስምምነቶች ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆኑን የማረጋገጥ እና የሥርዓተ-ፆታ ኢ-ፍትሃዊነት እንዳይፈጠር ይሰራል፡፡ ከአጋር አካላት ጋር በሚደረጉ ድርድሮች ላይ የሴቶች ተሳትፎ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

### *4.9.2 የአየር ንብረት ለውጥ*

ኢትዮጵያ ለከባቢ አየር ልቀትና ከባቢ አየር ለውጥ አነስተኛ አስተዋፅኦ ካደረጉ ሀገራት ተርታ ትጠቀሳለች፡፡ ድርቅ፣ በየብስ እና በውሃ ላይ ያለው ሙቀት መጨመር፣ የከባድ ዝናብ ክስተቶች ድግግሞሽ እና መጠን መጨመር እና የጎርፍ አደጋዎች እንዲሁም የአማካኝ የዝናብ መጠን መቀነስ ሁሉም በኢትዮጵያ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተጽኖዎች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹም ቀድመው በመከሰታቸው በሁሉም ዘርፍ የምርትና የንግድ ተወዳዳሪነትን በማዳከም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛል፡፡ በአየር ንብረት በዛባት የሚመጣውን ተፅዕኖ ሀገራችን በውል በመረዳት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ፕሮግራም ተነድፎ ባላፉት አራት ዓመታት ውስጥ በአረንጓዴ ኢኒሽቲቭ ሰፊ የደን ልማት ስራ በመሰራቱ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡ ስለዚህ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ መገንባት እና ሁሉንም ተጠቃሚና አሸናፊ ማድረግ የፖሊሲው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ የተጀመረውን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ለማስቀጠል እና ግቡን ለማሳካት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፡፡

- የአየር ንብረት ዝግጁነትና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን እንዲሁም የአካባቢ፣ የብዝሀ ህይወት እና ሥነ-ምህዳር ጥበቃን ከግምት ውስጥ በማስገባት የማምረት አቅምን እና ምርታማነትን በማሳደግ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል፡፡
- በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ ባለው ዓለም አቀፍ የትብብር ማዕቀፍ መሰረት የዝቀተኛ ካርቦን ኢኮኖሚን እንዲፋጠን ይሰራል፣ የከባቢ አየር ለውጥን ለመቋቋም (Climate Change Mitigation) ወደታዳሽ የሃይል ምንጮች ያሚደረገውን ለውጥ ያፋጥናል፣ የሀይል አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሳልጥ ሀይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ያስፋፋል፡፡
- የምርትና አገልግሎት ግብይት ሥርዓቱ የአካባቢ ደህንነትን እና የአየር ንብረት ሚዛንን በሚጠብቅ ሁኔታ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ በዝቅተኛ ካርቦን ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች የማበረታቻ ከፍያ ሥርዓት (Carbon Pricing) ይዘረጋል፡፡

### *4.9.3 ስራና ሰራተኛ*

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሠራተኞች መሠረታዊ መብቶችና የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ክልከላ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በ2011 አሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ከሰራተኛው ማህበረሰብ ጋር የተያያዙ የሰራተኛ መብቶች እና ግዴታዎች በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ የስራ እድል በአብዛኛው

በከተማ እና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ያተኮረ ነው፡፡ በተለይ በከተሞች ውስጥ ስራ የሌላቸው የህበረሰብ ክፍል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሲሆን በዚህ ዘርፍ ውስጥ አብዛኛው ህዝብ ሴቶች እና ወጣቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የሰራተኞች የክህሎት ደረጃ ዝቅተኛ መሆን ቁልፍ ፈተና ሲሆን በአገሪቷ ንግድ ላይም ተፅዕኖ አለው፡፡

- ስለሆነም መንግስት የንግድ ሥርዓቱን በማጠናከር በስፋት የስራ እድልን እንዲፈጥር ይደረጋል፡፡
- በዓለም አቀፉ የንግድ ሥርዓት የኢንዱስትሪዎች ዘላቂ ልማት የሚረጋገጠው ስራ እና ሰራተኛ ፍትሃዊ መስተጋብር እንዲኖራቸው ያስገደዳል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አሁናዊው የምርት እና ሸቀጦች ግብይት የህፃናት ጉልበት፣ የክፍያና የስራ ላይ ደህንነት ፣የስራ ከባቢ ምቹነት እና ሌሎችም ሰራተኛውን ያማከሉ መስፈርቶችን ደንግጓል፡፡ ስለሆነም መንግስት የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች በዚህ ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ የማሳደግ፣ የመቆጣጠር እና ጥረታቸውንም የመደገፍ ስራ ይሰራል፡፡

#### *4.9.4 የአካል ጉዳተኛ አካታችነት*

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸው ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግስት እና ሌሎች አካላት አካል ጉዳተኝነት በተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ውስጥ እንደ ሌሎች የህብረተሰብ አካላት ታይተው መካተት እንዳለባቸው ታምኖበት እየተሰራ ይገኛል፡፡ አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ዜጎች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ እነዚህን መብቶች መሰረት ያደረጉ አካሄዶች እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ወደ ህብረተሰቡ ሙሉ በሙሉ እንዳይቀላቀሉ የሚከለክሉትን መሰናክሎች ማስወገድ ወሳኝ እና ለድህነት ቅነሳ እና ለበለጠ ሁሉን አቀፍ እና ቀጣይነት ያለው ልማት ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

ምንም እንኳን አካል ጉዳተኞች ምቹ በሆነ አካባቢ ውስጥ ብዙ ስራዎችን የመስራት እና ውጤታማ የመሆን አቅም ያላቸው ቢሆኑም ብዙ ጊዜ በስራ ላይ መድልዎ ይደርስባቸዋል፡፡ ስለዚህ አካል ጉዳተኞችን በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የንግድ ሥርዓቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹና ተስማሚ እንዲሁም ድጋፍ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### 4.9.5 ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች

ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራ በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ሆኖም ግን እነዚህ ኢንተርፕራይዞች በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ትንሽ ነው። በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን ከሚያደርጉት ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ከፍተኛ የንግድ ወጪ መብዛት ነው። ወደ ውጭ የሚላኩ አብዛኞቹ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርት ከትላልቅ የንግድ ድርጅቶች ጋር ተመሳሳይ የንግድ እንቅፋቶች ያጋጥማቸዋል። ሆኖም ኢንተርፕራይዞች አብዛኛውን ጊዜ አነስተኛ ካፒታል ስላላቸው የውጭ ገበያ ለማግኘት መቸገር እና ለውስብስብ የቁጥጥር መስፈርቶች ምላሽ የመስጠት አቅማቸው አናሳ ነው። ስለዚህም የንግድ ሥርዓቱ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በዓለምአቀፍ የምርት ትስስር ውስጥ እንዲሳተፉ እና በወጪ ገበያ የላቀ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ድጋፍ ይደርጋል።

## 5. ቁልፍ የፖሊሲ ውጤቶች

የዚህ ንግድ ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማ ሀገራችን እያስመዘገበች ያለችውን ፈጣን፣ መሰረተ ሰፊ እና የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢኮኖሚ እድገት በማስቀጠል እና በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን የንግድ ልውውጥ በማስፋት በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ማስቻል ነው። በኢትዮጵያ ንግድን ለማስፋፋት እና ኤክስፖርትን ለማሳደግ ያለው አማራጭ የምርት ሂደትን፣ ምርታማነትን፣ ውጤታማነትን፣ አቅምን እና ተወዳዳሪነትን በመጨመር የወጪ ንግድን ማሳደግ ነው። ይህም የሁሉም ባለድሻ አካላት አስተዋጽኦ በማቀናጀት እንዲሁም በኢንዱስትሪው እና በኢንቨስተሮች መካከል ትስስር በማጠናከር የልማትና ድህነት ቅነሳ መንታ ዓላማዎችን ለማሳካት ጥቅም ላይ ይውላል።

የንግድ ፖሊሲው በሀገራዊ ልማት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ማለትም ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የወጪ ንግድ ብዝሀነትን ማስፋፋት፣ ፈጠራ እና የውጭ ንግድን ማበረታታት፣ የንግድ እድሎችን ማስፋት እና በሸማቾች እና በአምራቾች መካከል ያለው ሚዛን ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርት ላይ ያተኮሩ ድርጅቶችና እና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚያመርቱ ድርጅቶች ፍላጎት መካከል ያለውን ሚዛን ለማስጠበቅ ያለመ ነው። በዚህ ረገድ ከዚህ ፖሊሲ የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

**ውጤት 1፡ የዘመነ፡ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበት የሀገር ውስጥ ንግድ ሥርዓት**

*መንግሥት የሀገር ውስጥ ንግድ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለህብረተሰብ ኑሮ መሻሻል የሚያበረከተውን ጉልህ አስተዋፅኦ ከግምት በማስገባት እና ንዑስ ዘርፉ የገጠመውን አሁናዊ ውስብስብ ችግሮች በመፍታት የዘመነ፡ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበት የሀገር ውስጥ ንግድ ሥርዓት መገንባት የንግድ ፖሊሲው ከሚያሳካቸው ቁልፍ ውጤቶች አንዱ እንዲሆን ተደርጓል፡፡*

**ውጤት 2፡ ግልፅና ፍትሃዊ የገቢና ወጪ ንግድ አስተዳደር ማዕቀፍ**

*ሀገራዊ ኢንቨስትመንትን ለማሳብና ለማበረታታት፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች በዓለም ገበያ የሚኖራቸውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ጥራታቸው የተጠበቀና ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ ለማድረግና የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪነት ለመደገፍ የሚያስችል ግልፅነት ያለውና ፍትሃዊ የወጪና ገቢ ንግድ አስተዳደር ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የንግድ ፖሊሲው ውጤታማነት የሚረጋገጥበት አንዱ መለኪያ እንዲሆን ተደርጓል፡፡*

**ውጤት 3፡- የተሳለጠ የገቢና ወጭ ንግድ አሰራር**

በዚህ ፖሊሲ ተግባራዊነት ኢትዮጵያ የተሳለጠ የገቢና ወጪ ንግድ አሰራር በመተግበር በግብይቱ ላይ የጊዜ ብክነትን እና የሸቀጦችን የዋጋ ለመቀነስ ያስችላታል፣ ከኤክስፖርት የምታገኘውን ግቢ ይጨምራል፣ የግብይቱ ውስጥ የአቅርቦት ሰንሰለት የተሳለጠ ይሆናል፣ ጠንካራ የኢኮኖሚ እድገት እና የስራ እድል ይፈጥራል፣ እንዲሁም የተሻለ የገቢያ መዳረሻ እንድታገኝ እና ተወዳዳሪነትን ያጎለብታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**ውጤት 4፡- የገቢና ወጭ ምርትና አገልግሎቶች ጥራት ማረጋገጥ**

በዚህ ፖሊሲ ትግበራ ገቢ እና ወጪ ምርቶች እና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ተከትለው የሚዘጋጁበትን የደረጃ ዝግጅት ሥርዓት እንዲተገበር፤ ተናባቢነትም እንዲኖርው (harmonization) ይረዳል፤ የፍተሻ፣ የኢንስፔክሽን እና የሰርተፊኬሽን አገልግሎቶች በነዚሁ ደረጃዎች መስፈርት እንዲሰጡ እድል ይፈጥራል፤ እንዲሁም በወጪ ገቢው ንግድ ላይ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ስልጠና እና ትምህርት እንዲያገኙ ሲያስችል፤ ይኼም ገቢ እና ወጭ ምርቶች እና አገልግሎቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በማስቻል፤ የሸማቾች ጤንነት እና

ደህንነት እንዲጠበቅ፣ ፍትሃዊ የንግድ ሥርዓት እንዲሰፍን እና ሀገራችን በዓለም አቀፍ ገቢያ ተአማኒ የንግድ አጋር ሆና እንድትታይ ያደርጋል።

**ውጤት 5፡- በመጠን፣ በአይነት፣ በገቢ እና በመዳረሻ ገበያዎች ያደገ የወጪ ንግድ**

ይህ ውጤት የሚያመላክተው መዋቅራዊ እና ያተገባበር ተግዳሮቶቻችን በመፍታትና ሀገራዊ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ፣ ወጪ ንግድን የማስፋፋት እና የወጪ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠን እና በመዳረሻ ገበያ ለማሳደግ እና የወጪ ንግድ እድገትን እውን በማድረግ ረገድ የሚመዘገቡ ውጤቶችን ነው። በዚህ ፖሊሲ ኢትዮጵያ በኤክስፖርት መጠን ላይ ከፍተኛ እድገት እንደምታስመዘግብ፣የምትልከውን የሸቀጦች አይነት በማብዛት፣ ገቢን እንድታሳድግ እና ወደ አዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ታስፋፋለች ተብሎ ይጠበቃል። ኢትዮጵያ ምርትን በመጨመር እና በማስፋት፣ በባህላዊ የወጪ ንግድ ላይ እሴት በመጨመር እና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ገበያዎች በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ግኝቷን በማጠናከር በውስን ምርት ወይም የንግድ መዳረሻ ሃገር ላይ ያለውን ጥገኝነት ይቀንሳል። ይህም ኢኮኖሚያዊ ማገገምን ያጠናክራል፣ የንግድ ገቢን ያረጋጋል፣ቀጣይነት ያለው እድገትን ያረጋግጣል፤ ኢትዮጵያ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ተወዳዳሪእንድትሆን ያደርጋታል።

**ውጤት 6፡- በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር ውስጥ ያደገ ሚና**

በዓለም አቀፍ የምርት ትስስር (global production network) ዉስጥ የሚሳተፉ የሀገራችን አምራቾች ቁጥር መጨመር እና ከፍተኛ ዋጋ ሊያስገኙ የሚችሉ እሴት የተጨመረባቸው፣ ደረጃቸውን የጠበቀ ምርት በማምረት በዓለም አቀፍ ገበያ አስተማማኝ የገበያ እድል በመፍጠር የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ ነው።

**ውጤት 7፡- ለሸማቹ ፍትሃዊነትንና ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ምርትና አገልግሎት አቅርቦት**

ይህ ፕሮግራም የሸማቾች መብትን ለማስጠበቅ እና ፍትሃዊ ንግድን ለማሳደግ ብሎም ግልፅና ተገማች፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት እና ሥነ- ምግባራዊ የገበያ አካባቢ ለመፍጠር ይጠቅማል። ፕሮግራሙ ሸማቾችን ከብዝበዛ ፣ ከአሳሳች ድርጊቶች እና ደረጃቸውን ካልጠበቁ እና ጉዳት ላይ ከሚጥሉ ምርቶች እና አገልግሎቶች የሚጠብቅ ሲሆን በሌላ ጎኑ ፍትሃዊ ንግድን ያበረታታል። በዚህም የሸማቾችን መብት የሚጠብቁ የህግ ማዕቀፎች በማጠናከር ሸማቾችን ስለመብታቸውና ስላላቸው የህግ ጥበቃ፣ ጥራት ያላቸውን ምርቶች እና አገልግሎቶች መጠቀም የሚያስችላቸውን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል። እንዲሁም ፕሮግራሙ አላግባብ የንግድ

እንቅስቃሴዎችንና የዋጋ ጭማሪዎች ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ባለድርሻ አካላት ስለ ዓለም አቀፍ የሸማቾች መብት ጥበቃ ደረጃ በቂ ግንዘቤ እንዲኖራቸውና እንዴት በእኩል ደረጃ መስራት እንዳለባቸው የማብቂያ ስራ ይሠራል፡፡ ፕሮግራሙ ፍትሃዊነትን እና ኃላፊነትን በማረጋገጥ የሸማቾችን እምነት እንዲያድግ እና ሚዛናዊ እና ፍትሃዊ የገበያ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

### ውጤት 8፡- ፍትሃዊ፣ተገማች እና ውድድር የሰፈነበት የግብይት ሥርዓት

ይህ ውጤት ትኩረቱን የሚያደርገው ሸማቹ ማህበረሰብ ጥራቱን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት መግኘቱን መረጋገጥ ላይ ነው፡፡ ይህም ሲባል በገበያ ውስጥ ግልፅ የሆነ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት እና የንግድ ሥርዓቱ ከምርት ጀምሮ እስከ ስርጭት ብሎም ተጠቃሚው ድረስ ሥነ- ምግባርን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም የሸማቹን ማህበረሰብ ደህንነቱ ተጠብቆ፣ የመግዛት አቅም ተገናዝቦ፤ ምርቶች በበቂ ሁኔታ በገበያ ላይ መቅረባቸው እና ያልተጭበረበሩ መሆናቸውን በማረጋገጥ የሸማቹን እርካታ እና እምነት ከፍ እንዲል ማድረግ ነው፡፡

## 6. የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ

ፖሊሲው የሀገራዊ ልማት እቅድ ግቦች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን በዋነኝነት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ የወጪ ንግድ ምርቶችን ማስፋፋት፣ ፈጠራና ለሁሉም ክፍት የሆነ ነጻ የንግድ ሥርዓትን ማበረታታ፣ የንግድ እድሎችን ማስፋትና ንግድ በማሳለጥ ከድንበር በፊት፣ በድንበር ላይ እና ከድንበር በኋላ ያሉ መሰናክሎችን ማስወገድ የሚሉትን የሚጨምር ነው፡፡ ስለዚህ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈጻሚ የመንግስት አካላት ፖሊሲውን የማስፈጸምና የመከታተል፤ የንግዱ ማህበረሰብ በተቀመጡ አሰራሮችና መለኪያዎች መሰረት የመተግበር እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብና የምርምር ተቋማት የሌሎቹን የማህረሰብ ክፍሎች ፍላጎት በጥናትና በአድቮከሲ ስራዎች ፓሊሲዎችን እንዲያውቋቸው የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ፖሊሲውን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሚሆኑ የህግ ማዕቀፎች እና የልማት ፕሮግራሞችን በመለየት ወደ ትግባር መግባት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 6.1 ፈፃሚ ተቋማት

ምንም እንኳን አዋጁ በግልጽ ለንግድ ፖሊሲ ቀረጻ ዋነኛ ኃላፊነት ያለበት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ቢሆንም ሌሎችም ተቋማት በኢትዮጵያ ንግድ ፖሊሲ ቀረጻና ትግበራ ላይ

ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጪ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሰርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤ ያፀድቃል እንዲሁም ይተገብራል፡፡  የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የሀገሪቱን የውጪ ንግድ እና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጪ ኢንቨስተሮችን መለየትና መሳብ፣ መፈለግ፣ የቴክኖሎጂ ምርጫና ሽግግር ማድረግ፣ ከውጪ ምንጮች የፋይናንስና ቴክኒክ ድጋፎች እንዲመጡ ለማድረግ በዲፕሎማሲ ዘርፉ የመንግስት አስፈፃሚ አካል ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር በበኩሉ "ቁጠባ፣ ኢንቨስትመንት እና የገቢና የወጪ ንግድ የኢኮኖሚ ግቦችን በማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፡፡ በተጨማሪም የክልል የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያቤቶች እና ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ፖሊሲውን በማስፈፀም የላቀ ድርሻ አላቸው፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሌሎች የመንግስት አካላት በሙሉ ለንግድ ፖሊሲው ትግበራ እና/ወይም ፖሊሲ ቀረጻ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር ተባብረው የመስራት ኃላፊነት ያለባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ የሚከተሉት ጉዳዮችም በትኩረት መተግበር አለባቸው፡፡

**በሚኒስቴር መ/ቤቶችና ድርጅቶች መካከል ያለውን ትብብር ማሻሻል፦**

የኢትዮጵያ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በፖሊሲ ቀረጻ  ከዘመናዊ ዓለም አቀፍ ንግድ ጋር የመተሳሰር፣ ከውጪ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የፊሲካል ፖሊሲ ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሌሎች በርካታ የመንግስት ተቋማት በንግድ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ ወይንም በትግበራው ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ እነርሱን የፖሊሲ ቀረጻ ተግባር ላይ ሲሳተፉ ካለባቸው ኃላፊነት አንጻር በተደጋጋሚ ውይይቶች ማደረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም ምናልባት አሁን በተግባር ላይ ያለውን በሚኒስቴር መ/ቤቶች ያለውን የአሰራር ሂደት እና ትብብር ስነ ሥርዓት እንዲሁም የሰው ሀብትና የፋይናንስ ድንጋጌዎችን ማሻሻል ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዋነኛ ግባቸው ከንግድ ጋር ያልተገናኙ ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች/ኤጀንሲዎች ግልጽ የሆነ ኃላፊነት እና ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

**የኢምባሲዎችን እና የሀገሪቱን የውጪ ሚሲዎኖችን መጠቀም፦** በብዙ ሀገሮች የውጪ ኢምባሲዎቻቸውን እና ጽ/ቤታቸውን ለድርጅቶቻቸው ስለ ዓለም አቀፍ ንግድ ሥርዓት ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና በቂ መረጃ እንዲያገኙና የንግድ እድሎችን ለመፍጠር እንደሚጠቀሙበት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ሊተገበር የሚችለው በኢምባሲዎች ውስጥ ንግድና ኢንቨስትመንት

የሚያስፋፉ ጽ/ቤቶችን በመመስረት ነው፡፡ ከኤክስፖተሮች እና ከኢምባሲ ባለስልጣናት ጋር ቀጥተኛ ትስስር በመፍጠርና በመገናኘት የኢትዮጵያ ኢምባሲዎች እና ሌሎች ሚሲዮኖች ለኢትዮጵያ ንግድ ዘርፎች የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎችን የማስፋፋት እንዲሁም የውጪ ንግድ ኢንቨስትመንት ለማግኘት የንግድ ባዘሮችና ትዕይንቶችን በማዘጋጀት ማስተዋወቅ ይገባል፡፡

**ተጨማሪ አጋር አካላትና ሚናዎቻቸው፡-** የንግድ ፖሊሲ የቀረጻ ሂደት ትግበራና ቁጥጥር ስራ በርካታ አጋር አካላትን የሚያሳትፉ ሂደቶች ናቸው፡፡ እነሱም የንግድ ድርጅቶች፣ ሰራተኞች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ ግብርና፣ አገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች፣ ቸርቻሪዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የአካባቢና የጥበቃ ድርጅቶች እና የሸማች ጥቅም የሚያስከብሩ ሲቪል ማህበራት፣ ሚዲያዎች እና የምርምር ተቋማት ይገኙበታል፡፡ ለንግድ ፖሊሲው ስኬታማነት አጋር አካላት በፖሊሲዎች ድርድርና ትግበራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የንግድ ፖሊሲ ትግበራ ላይ አጋር አካላት ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻል ጥረት ይደረጋል፡፡

### 6.2የህግ ማዕቀፍ

አዳዲስ ህጎችን ማዘጋጀት እና በስራ ላይ ያሉትን አዋጆች እና ደንቦች በዝርዝር ማየት እና መከለስ የሚኖሩባቸውን መከለስ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 (ማሻሻያ)
- የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 (ማሻሻያ)
- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር550/1999 ደንብ (ማሻሻያ)
- የቅባት እህሎችና የጥራጥሬ ግብይት ደንብ (ማሻሻያ)
- አጋር አካላት እንዴት በይፋ ማሳተፍ እንደሚቻል መመሪያ ማዘጋጀት፡፡

### 6.3 ልማት ፕሮግራሞች

የፖሊሲውን ቁልፍ ውጤቶች ለማሳካት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መደበኛ በጀት የሚጠቀም ቢሆንም ተጨማሪ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁ አዳዲስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ማቋቋም፣ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን መገንባት፣ መሰረታዊ ጥናትና ምርምር በማድረግ የድርድር ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ የሰው ሃይል አቅም ግንባታ እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ

ያላቸው የሀገሪቱን ወጪ ምርቶች ለማስተዋወቅ ኢግዚቢሽኖችን እና ኤክስፖዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስራዎች በተነጻጻሪነት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁ በመሆኑ የሚከተሉት የልማት ፕሮግራሞች ተለይተዋል፡፡

**ፕሮግራም 1፡- የአገልግሎት አሠጣጥና የቁጥጥር ሥርዓት ግንባታ ፕሮግራም**

የዘመነ፡ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበት የሀገር ውስጥ ንግድ የሀገር ውስጥ ንግድ አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው መንገድ እንዲከናወን፤ ህገ ወጥነትና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ አሠራሮችን ለመቆጣጠር የሚያስቸል በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአገልግሎት አሠጣጥና የቁጥጥር ሥርዓት ተሻሽሎና ተጠናክሮ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የንግድ ሥራን ለመጀመርና በዘላቂነት ውጤታማ ሆኖ ለመቀጠል የሚያስችል ምቹ አስተዳደራዊና ሬጉላቶሪ ከባቢያዊ ይፈጠራል፡፡

**ፕሮግራም 2፡- የገበያ መሰረተ ልማት እና መረጃ ሥርዓት ግንባታ ፕሮግራም**

የሀገር ውስጥ ገበያዎችና የግብይት ሰንሰለቶች ቀልጣፋ፤ ተዳራሽና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የዘመናዊ ገበያ ማዕከላትና የግብይት መሠረተ ልማት ግንባታና የመረጃ ሥርዓት ዝርጋታ፤ የአቅርቦትና የእሴት ሰንሰለት ትሥሥር ፕሮግራም የፖሊሲው ማስፈፀሚያ መሳሪያዎች ይሆናሉ፡፡

**ንኡስ ፕሮግራሞች፦**

- የዲጂታል ንግድ እና ኢ-ኮመርስ ንዑስ ፕሮግራም፡፡
- የግብርና ምርቶች ገበያ መሰረተ ልማት ንዑስ ፕሮግራም፡፡
- የወጪ ምርቶች ግብይት መሰረተ ልማት ንዑስ ፕሮግራም፡፡

**ፕሮግራም 3፡- አማራጭ የግብይት ሥርዓት ግንባታ ፕሮግራም**

መንግሥት የገበያ ጉድለትን ለማረምና ገበያን ለማረጋጋት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል አምራቹንና ሸማቹን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል ከነፃ ገበያ ትይዩ የሆነ በሚታወቅ ህግና አሠራር የሚመራ አማራጭ የግብይት ሥርዓት ዝርጋታ ፕሮግራም ይተገባራል፡፡

## ፕሮግራም 4፡- በወጪና ገቢ ኮሪደር የተቀናጀ የጠረፍ አስተዳደር ልማት ፕሮግራም

በወጪ እና ገቢ ንግድ ኮሪድሮች ያሉ መሰናክሎች የንግድ ልውውጡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳርፉ ይታያል፡፡ በደንበር ላይ የሚደረጉ ፍተሻዎች፤ በባህርና በደረቅ ወደቦች የሚከናወኑ የጉምሩክ ሥነሥርዓቶች ቅልጥፍና የሚጎድላቸው መሆኑ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የላላ መሆን ወጪ ምርቶቻችን በሀገር ውስጥ ገበያም ሆነ በወጭ ሀገር ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ሲያደርጋቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትም ከአቅርቦት እና ከጥራት ጋር ተያይዞ ውሱንነት ሲታይባቸው ታይቷል፡፡ ስለዚህ በወጪና ገቢ ኮሪደር የተቀናጀ የጠረፍ አስተዳደር ልማት ማካሄድ በበርካታ መ/ቤቶች ቅንጅት እንዲፈጠር፣ ሰራተኞች ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣ የጉምሩክ ሥርዓቱ የተሳለጠ እንዲሆን፣ እና አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን እንዲገነቡ፤ ብሎም የወጪና ገቢ ንግድ እንቅስቃሴ መዘግየትን ለመቅረፍ ያግዛል፡፡

### ንኡስ ፕሮግራሞች፡

- የጉምሩክ አሰራር ሂደቶች ውህደት እና ማሻሻል ንኡስ ፕሮግራም
- የመሰረተ ልማት፣ የአሰራር ሥርዓት እና የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ንኡስ ፕሮግራም
- የተቀናጀ የደረጃዎች እና የቴክኒክ ደንቦች ትግበራ ንኡስ ፕሮግራም

## ፕሮግራም 5፡- ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጣናዊ ንግድ ትስስርና ውህደት ትግበራ ፕሮግራም

ይህ ፕሮገራም የገበያ ተደራሽነትን የሚያሳድጉ ስትራቴጂካዊ ፖሊሲዎችን እና ውጥኖችን በመተግበር፣ የወጪ ንግድ ብዝሃነትን በማጎልበት እና ኢኮኖሚያዊ ውህደትን በማሻሻል የኢትዮጵያን የንግድ ግንኙነት በዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ቀጣናዊ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡ መርሃ ግብሩ ከኢትዮጵያ የልማት ግቦች ጋር በመቀናጀት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ገበያ ያላትን ሚና በማጠናከር (እንደ ዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅት)፣ ከአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) የሚገኘውን ጥቅም በማመቻቸት እና እንደ ኮሜሳ እና ኢጋድ ካሉ ድርጅቶች ጋር ቀጣናዊ የንግድ ትብብርን ማሳደግ ላይ ያተኩራል፡፡

### ንኡስ ፕሮግራሞች፡

- የ WTO እና AfCFTA ትግበራ እና የንግድ ማቀላጠፍ ንኡስ ፕሮግራም
- የቀጣናዊ የንግድ ትብብር ፕሮግራም (ኮሜሳ እና ኢጋድ) ንኡስ ፕሮግራም

- የተቋማዊ አቅም ግንባታ እና የፖሊሲ ድጋፍ ንኡስ ፕሮግራም
- ወደ ውጪ የመላክ ዝግጁነት ንኡስ ፕሮግራም

**ፕሮግራም 6፡- የወጪ ንግድ ገበያ ማስፋፊያ እና ብዝሃነት ፕሮግራም**

የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ በመጠን፣ በአይነትና በጥራት ውስን ከመሆኑ ባሻገር በግብርና የወጪ ምርቶች ላይ እጅጉን ጥገኛ ነው፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት ዘርፍ የወጪ ንግድ ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነም የታወቀ ነው፡፡ የምርቶቹ/አገልግሎቶቹ በአይነትና በዘርፍ የተወሰኑ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የጥራትና የመጠን ውስንነቶችም አሉባቸው፡፡ በተመሳሳይ የገበያ ሥርዓትና የገበያው ተዋንያን የወጪ ምርቶችን ምርታማነትና ብዝኃነትን ለማሳደግ በሚያስችል ቁመና ላይ እንዳልሆኑም በርካታ አመላካቾች አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆንም ዓለምአቀፋዊና ቀጣናዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም መጪውን የንግድ ምህዳር ታሳቢ ያደረገ የወጪ ንግድ ገበያ ማስፋፊያ እና ብዝኃነት ፕሮግራም ነድፎ መተግበር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**ፕሮግራም 7፡- በዓለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚሳተፉ የምርትና ሀገርግሎት ዘርፎች አቅም ግንባታ ፕሮግራም፡፡**

በዓለም አቀፍ እሴት ሰንሰለት ውስጥ ለማሳተፍ የሚቻልባቸው ዘርፎች እና ያሉ እድሎችን ለመለየት የሚያስችሉ ምርምሮችና ጥናት ስራዎችን መስራት እና ግል ተቋማትን በብቃት እንዲሳተፉ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራ ለመስራት ነው፡፡

**ፕሮግራም 8፡- የሸማቾች መብት እና ፍትሃዊ ንግድ ማረጋገጥ ፕሮግራም**

የንግድ ሥርዓታችን ፍትሃዊ ውድድር የሰፈነበትና የሸማቹንና የነጋዴውን መብትና ጥቅም የሚያስከብር እንዲሆን ለማድርግ የንግድ ወድድርና የሸማቾች መብት ጥበቃ ህጎችን የማሻሻልና ዝርዝር የማስፈፀሚያ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲኖሩት የማድረግና ጠንካራ አስፈፃሚ አካል በማደራጀት የፖሊሲውን ዓላማ ለማስፈፀም ይህ ፕሮግራም ተነድፎ በሰነዱ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

### 6.4 የፖሊሲ ክትትልና ግምገማ

መንግስት በተለያዩ ጊዜያት ሰፊና ጥልቀት ያላቸው የንግድና ኢንቬስትመንት ስምምነቶችን አድርጓል፡፡ እነዚህ የተፈረሙ የንግድ ስምምነቶች እና ፖሊሲዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው

ለማረጋገጥ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ማሻሻያ የሚደረግበት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የተፈረሙ የንግድ ስምምነቶችንና ፖሊሲዎችን አፈጻጸም በየጊዜው በተደራጀ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መተግበር በሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ ከስምምነቶቹ የሚገኘውን የንግዱን ማህበረሰብ፣ የሰራተኞችና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማሳደግ የሚያስችል የድርድር ሀሳቦችን ለማመንጨት ይረዳል።

የንግድ ስምምነቶችን እና ፖሊሲዎችን መከታተል ማለት ፖሊሲዎቹ እና ስምምነቶቹ በምን ያህል ደረጃ በትክክል እየተተገበሩ መሆኑን መለየት ነው። በሌላ በኩል ግምገማ ማለት የተፈረሙ የንግድ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ያስገኟቸውን ተጽእኖ እና የተመዘገቡ ውጤቶችን መመርመር ወይም መፈተሽ ነው። በመሆኑም የንግድ ስምምነቶች እና ፖሊሲዎች የተቀመጠላቸውን አላማና ግብ በማሳከት ለንግዱ ማህበረሰብ፣ ለሸማቾች እና ለሰራተኞች ያስገኙትን ጥቅም መመርመር አስፈላጊ ይሆናል።

የስምምነቶችና ፖሊሲዎች ያሳደሩትን ተጽዕኖ ለመከታተተልና ለመገምገም የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማዘጋጀት በመጀመሪያ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ቢሆንም በሂደት ግን በተዘጋጀው የክትትልና ግምገማ ሞዴል መጠነኛ ማስተካከያዎችን ብቻ በማድረግ ወደፊት በሚደረጉ በርካታ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ላይ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

የንግድ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ክትትልና ግምገማ ስፋትና ጥልቀት በአጠቃላይ መርሆዎች ላይ የሚመሰረት ሲሆን በተለይም ስምምነቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ አንዳንድ ስምምነቶች ከአንድ ሀገር ጋር የተወሰኑ የገበያ እድሎች ላይ የሚደረጉ የሁለትዮሽ ሲሆኑ ሌሎች ስምምነቶች ደግሞ በበርካታ መንግስታት በአህጉር ደረጃ የሚደረጉ እንደ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ስምምነት (AfCAFTA) የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ሁለት ስምምነቶች የሚያስፈልጋቸው የክትትልና ግምገማ ይዘት ይለያያል። ለመጀመሪያው ስምምነት ጥቅል አመላካቾች እና መለኪያዎችን መጠቀም በቂ ነው።

የንግድ ስምምነቶች በበርካታ የኢኮኖሚ ክፍሎች ላይ የሚከናወኑ ሲሆኑ በንግዱ፣ በሸማቹ እና በሰራተኞች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ ለመቀነስ ሲባል ሰፊ ጊዜ የሚወስዱም ናቸው። ስለዚህ ክትትሉና ግምገማው ቅድሚያ ትኩረት ሊያደርግበት የሚገባው አንደኛ የፖሊሲዎቹን ተጽእኖ መቼ ማጥናት እንደሚያስፈልግ ሁለተኛው በተለያዩ የጊዜ አድማሶች ምን አይነት ጥያቄዎችና ዘዴዎች ያስፈልጋሉ እና በመጨረሻም ተጽእኖን ለማጥናት ምን አይነት ስልቶች ያስፈልጋሉ የሚሉት ወሳኝ ናቸው።

የንግድ ፖሊሲ ተጽዕኖን ለማጥናት በሶስት የጊዜ አድማሶች በአጭር ፣ በመካከለኛ እና ረጅም ጊዜ በመወሰን ክትትልና ግምገማው ማከናወን ያስፈልጋል። የንግድ ፖሊሲን ለማሻሻል በሚደረገው ግምገማ እና ፍተሻ ገላጭ የሆኑ ጥናት ዘዴዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡ በጊዜ ሂደት የበለጡ መረጃዎች የሚገኙ ሲሆን በመካከለኛና ረጅም ጊዜ ጥናት ላይ መደበኛና ኢኮኖሜትሪክስ ትንተና ዘዴዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።

በተጨማሪም የፖሊሲው አላማዎች ተፈጻሚ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለካት የሚያስችሉ የመለኪያ ዘዴዎች ያስፈልጋሉ። ፖሊሲው ያመጣውን ተጽእኖ ለመለካት የወጪ እና ገቢ ንግድ አመላካቾች ብቻ በቂ ስለማይሆኑ ሌሎች ተጨማሪ የኢኮኖሚያዊ ውጤቶች (ለምሳሌ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትምንት FDI) ፣ ማህበራዊ ግምገማዎች (ለምሳሌ የሥራ እድል፣ ደመወዝ እና የነፍስ ወከፍ ገቢ) የከባቢያዊ ግምገማዎች (ለምሳሌ የበካይ ጋዞች መለቀቅ፣ የአየር ብክለት፣ ብዝሃ ህይወት፣ የውሀ ሀብትና ጥራት) በሰውና በመሰረታዊ የሰራተኛ መብት ጥናት ላይ የተመረኮዙ ሊሆኑ ይችላሉ።

የንግድ ፖሊሲው ያመጣውን ተጽዕኖ ለመገምገምና ለማጥናት የተለያዩ አይነት አቀራረቦችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። አሁናዊ የንግድ ስምምነቶች ተፈጻሚ የሆኑ ታሪፎችን በመቀነስ ብቻ ሳይወሰኑ በርካታ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በማካተት እስከ 10 ዓመት እድሜ ሊራዘሙ የሚችሉ ይሆናል።። በዚህ ጊዜ ውስጥ በርካታ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ምክንያቶች ንግድና ኢንቨስትመንቱ ላይ ተጽእኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ። የንግድ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ተጽእኖ በውጤት በሚለካበት ጊዜ ግልጽ የሆነ መለያና መተንበያ ዘዴዎች ሊኖሩ ይገባል። ስለዚህ  ወጥ የሆነ የአመልካቾች መረጃ አያያዝ ዘዴ፣ አቀራረብ የንግድ ፖሊሲው እርምጃዎችና የተገለጹ አላማቸውን ማሳካታቸውን እና አለማሳካታቸውን የሚለካበት ገላጭ ስታቲስቲካል ሞዴሎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ስለሆነም ሶስት ዘዴዎችን ማለትም ገላጭና የተተነተኑ መረጃዎች፣ ኢኮኖሜትሪክስ ሞዴሊንግ እና የመጠን መለኪያ አቀራረብ ማለትም ቅኝትን፣ ቃለ-መጠይቆችን፣ የኬዝ ጥናቶች፣ ወርክሾፕና ምክክሮች በማካሄድ መረጃ ይሰበሰባል። ሁሉም አቀራረቦች አስፈላጊና በተለያየ ጊዜ አድማሶች ሊተገበሩ የሚችሉ ሆኖ አስተማማኝ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ጥቅል የሆነ የኢኮኖሚ መረጃዎችን መሰብሰብ የንግድ ፖሊሲዎችን ለመገምገም ለመከታተል እና ለመከለስ በጣም ወሳኝ ነው።

## 7. ፖሊሲውን የማውጣት ስልጣን እና የፖሊሲው ወሰን

የንግድ ፖሊሲው በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስተባባሪነት የሚመለከታቸውን የመንግስት መስሪያ ቤቶች በማሳተፍ ተዘጋጅቶ ለፕላንና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ቀረቦ አሰተያየት ከተሰጠበት በኋላ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቋል፡፡ ንግድ በባህሪው ሁሉንም አካላት የሚያሳትፍ እና የሚመለከት በመሆኑ በፖሊሲው የተቀመጡትን ጉዳዮችና አቅጣጫዎች ሁሉም የሚመለከተው የመንግስት ተቋማት፣የንግዱ ማህበረሰብ፣ የተለያዩ የንግድ ማህበረሰብ ሲቪክ ማህበራትና አደረጃጀቶች እና መላው ህዝብ ለተፈፃሚነቱ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ይሆናል፡፡

የንግድ ፖሊሲው በሀገሪቱ በወጣው የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 መሰረት ለንግድ ስራ በተፈቀዱ ምርትና አገልግሎቶች ሁሉ በመላ ኢትዮጲያ በሚከናወኑ የሀገር ውስጥ ንግድ ስራዎች፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሚደረግ የደንበር ንግድ እንዲሁም የወጪ ንግድ ስራዎች ሁሉ ይተገበራል፡፡ ፖሊሲው የሀገሪቱን የልማት ፖሊሲ በሚያፋጥን መልኩ የሀገር ውስጥና የወጪ ንግድን የማዘመን፣ የወጪ ንግድ ፖሊሲ የማዘጋጀት ሀላፊነት ያለው የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ቢሆንም በንግድ ፖሊሲው ዝግጅትና ትግበራ የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ትብብርና ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በንግድ ድርጅቶች፣ በአነስተኛ የንግድ ድርጅቶችና በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በአምራች ኢንዱስትሪውና በግብርናው ዘርፍ፣ በአገልግሎት ሰጪ ዘርፍ፣ በቸርቻሪ ነጋዴዎች፣ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የተሰማሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ከሸማቹ ህብረተሰብ ፍላጎትና ጥቅም አኳያ የተደራጁ የሲቪል ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የጥናትና ምርምር ተቋማት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ ስለሆነም ፖሊሲው የንግድን ሁሉን አቀፍ ሴክተራል ባህሪ በመረዳት የፖሊሲ ቅንጅትንና ወጥነትን ለማረጋገጥ ቀረጻው ከሌሎች ሀገራዊና ሴክተር ፖሊሲዎች ጋር እንዲተሳሰር ተደርጓል፡፡ የፖሊሲው ተፈፃሚነትም በንግዱ ማህበረሰብ፣ ንግድ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ሁሉ ይተገበራል፡፡

## 8. ተያያዥ ፖሊሲዎች

ንግድ በባህሪዉ ለሰው ልጅ ፍላጎት የሆኑ ሁሉንም ምርትና አገልግሎቶች አምራቾች፣ አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎችን የሚመለከት በመሆኑ የንግድ ፖሊሲ ከሀገራዊ ፖሊሲዎች ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡

**ከኢኮኖሚና የመሰረተ ልማት ፖሊሲዎች፣**

የንግድ ፖሊሲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኢኮኖሚና የመሰረተ ልማት ፖሊሲዎች ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ለፖሊሲው አፈጻጸምና አተገባበር ውጤታማ በመሆንና ባለመሆን ሂደት ውስጥ የዚህ ዘርፍ ፖሊሲ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው፡፡ የንግድ ፖሊሲ ትግበራ ሰፊ የምርትና አገልግሎት አቅርቦት እና የተሳለጠ መሰረተ ልማት መስፋፋት እንዲሁም በቂ እና የተሳለጠ የፋይናንስ አቅርበትና ሥርዓት የሚጠይቅ በመሆኑ ከዚህ ዘርፍ ፖሊሲ ጋር በተለይም ከግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ፣ከፋይናንስ ፖሊሲ፣ ኢነደስትሪ ፖሊሲ፣ ከኢንተርፕራይዝ ልማት ፖሊሲ፣ የከተማና መሰረተ ልማት ፖሊሲ እና ከጥራት ፖሊሲ ጋር የሚኖረው ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡

**የማህበራዊና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች**

የንግድ ፖሊሲ ለመተግበር የሰለጠነ እና ጤንነቱ የተጠበቀ የሰው ሃይል እና ህግና ሥርዓትን የተከተለ የውድድር መንፈስ መረጋገጥን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ከማህበራዊና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ለፖሊሲው አፈጻጸምና አተገባበር ውጤታማ በመሆን በዚህ ዘርፍ ካሉት ፖሊሲዎች መካከል የትምህርት ፖሊሲ እና የጤና ፖሊሲ ጋር ከፍተኛ ተያያዥነት አለው፡፡

**ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎች**

የንግድ ፖሊሲ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎች ጋር ያለው ግንኙነት ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይም የንግድ ሥርዓቱ ፍትሃዊ፣ የተሳለጠ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡ የምርትና አገልግሎት አቅርቦትና የመረጃ ሥርዓቱ የተቀላጠፈ እና ተደራሽ እንዲሆን፣ የምርትና አገልግሎት መዳረሻ ሀገራት ፍላጎት ለመለየት እና በወቅቱ ተወዳዳሪ ሁኖ ለማቅረብ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ውጭ የሚታሰብ ባለመሆኑ በዚህ ዘርፍ ያሉ ፖሊሲዎች ከንግድ ፖሊሲ ጋር የሚኖረው ትስስር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

## 9. የቃላት ፍች

- የመቀበል አቅም፦ የአንድ ድርጅት አዳዲስ እውቀት አስፍላጊነትን የመለየት፣ የማዋሃድ እና የንግድ ስራ ለማድረግ መቻል ነው።

- የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና (AfCFTA)፡ በመላው አፍሪካ ወደ 1.3 ቢሊየን ለሚጠጉ ሰዎች የሸቀጦች እና አገልግሎቶች አንድ ገበያ በመፍጠር እና የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊ ውህደት በማጠናከር በዓለም ትልቁን የነፃ ንግድ ቀጣና ለመመስረት ትልቅ ፍላጎት ያለው የንግድ ስምምነት ነው።

- የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች፡- በሁለት ወገኖች እና ከሁለት በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል ስምምነትን የሚያካትት የንግድ ስምምነት ነው።

- የውድድር ጥቅሞች፡- አንድ ሀገር ወይም ኩባንያ ከተወዳዳሪዎቹ በተሻለ ወይም በርካሽ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን እንዲያመርት የሚፈቅዱ ነገሮችን ያካትታል።

- ተወዳዳሪነት፡- ከሌሎች ኩባንያዎች፣ አገሮች፣ ድርጅቶች ጋር በተሳካ ሁኔታ መወዳደር የመቻል እውነታ ነው።

- ዲጂታል ንግድ፡- በኤሌክትሮኒክስ መንገድ በቴሌኮሙዩኒኬሽን እና/ወይም በአይሲቲ አገልግሎት የነቃ ንግድን የሚያመለክት ሲሆን በሁለቱም እቃዎችና አገልግሎቶች ንግድን ይሸፍናል።

- የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት፡- ከውጪ ሀገራት ይልቅ በአንድ ሰው ኩባንያዎች እና ምርቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ።

- የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI)፡- ድንበር ተሻጋሪ የኢንቨስትመንት ምድብ ሲሆን በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለ ባለሀብት ዘላቂ ፍላጎት ያለው እና በሌላ ኢኮኖሚ ውስጥ ባለው የድርጅት ነዋሪ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድርበት ነው።

- በዓለም አቀፍ የማምረት ትስስር (GPN) መሳተፍ፦ የተወሰነ ምርት ወይም አገልግሎት በማምረት ሂደት እና እስከ ተጠቃሚው እስኪደርስ ድረስ የሚከናወኑ ተግባራት ትስስር ማለት ነው።

- የመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP)፡- በመንግስት እና በግሉ ሴክተር ተቋማት መካከል የረጅም ጊዜ ዝግጅት ነው፡፡
- አህጉራዊ ውህደት፡- ሰላም፣ መረጋጋትና ሀብትን ለማስፈን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች ተባብረው ተቀራርበው ለመሥራት የተስማሙበት ሂደት ነው፡፡
- የንፅህና እና የዕፅዋት ጤና ጥበቃ (SPS) ፡- እርምጃዎች የሰውን፣ የእንስሳትን ወይም የእፅዋትን ህይወትን ወይም ጤናን ከተባይ እና ከበሽታዎች መግቢያ፣ መመስረት እና መስፋፋት እንዲሁም ተጨማሪዎች ፣ መርዛማዎች እና አደጋዎች ከሚመጡ አደጋዎች ለመጠበቅ የሚተገበሩ የኳራንቲን እና የባዮሴኪዩሪቲ እርምጃዎች ናቸው፡፡
- የታሪፍ እና የታሪፍ ያልሆኑ እንቅፋቶች፡- የታሪፍ እገዳዎች በመንግስት ታክስ ወይም ቀረጥ የሚጣሉት ከውጭ በሚያስገቡት ምርቶች ላይ ነው፡፡ ከታሪፍ ውጪ የሆኑ እገዳዎች መንግስት ከውጭ በሚያስገቡት ምርቶች ላይ ከጣለው ታክስ በስተቀር ሁሉንም ገደቦች ይሸፍናል፡፡
- የንግድ ቴክኒካል መሰናክሎች (TBT)፡- የግዴታ ቴክኒካል ደንቦችን እና አንድ ምርት ሊኖረው የሚገባውን ልዩ ባህሪያት የሚገልጹ እንደ መጠኑ፣ ቅርፅ፣ ዲዛይን፣ መለያ ማድረጊያ/ማሸግ/ማሸጊያ፣ ተግባራዊነት ወይም አፈጻጸምን የሚገልጹ የፍቃደኝነት ደረጃዎችን ያመለክታል፡፡
- ንግድ፦ በጅምላም ሆነ በችርቻሮ፣ በሀገር ውስጥ ወይም በአገሮች መካከል ሸቀጦችን የመግዛት፣ የመሸጥ ወይም የመለዋወጥ ተግባር ወይም ሂደት ነው፡፡
- የንግድ ነፃነት፡- በአገሮች መካከል የሚደረጉ የነፃ የሸቀጥ ልውውጥ ገደቦችን ማስወገድ ወይም መቀነስ ነው፡፡ እነዚህ መሰናክሎች ታሪፎችን፣ እንደ ግዴታዎች እና ተጨማሪ ክፍያዎች፣ እና ታሪፍ ያልሆኑ እንቅፋቶችን፣ እንደ የፍቃድ አሰጣጥ ደንቦች እና ኮታዎች ያካትታሉ፡፡